ወርኃዊ ጥንቅር፣ ቁጥር. 011
ታኅሣሥ 2018 ዓ.ም.



# የኢትዮጵያ እንደራሴዎች ክራሞት

እንደራሴ

እንደራሴ በብሪጅ ሪሰርች እና ኢኖቬሽን በየወሩ እየተዘጋጀ ይቀርባል።

research@bridge-et.org

BRIDGE Research & Innovation-
Parliaments. Peace. Policy

+251 911 86 12 34
+251 115 57 74 96
research@bridge-et.org
https://bridge-et.org/
150096, Addis Ababa, Ethiopia.
Kazanchis, across the main gate of UNECA, SA Building, 9th Floor, Office No. 5, Addis Ababa.

## መልክዓ-ብሪጅ

መቀመጫውን አዲስ አበባ ያደረገ፣ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ዐዋጅ ቁጥር 1113/2011 መሰረት አገር በቀል የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅት ሆኖ የተመዘገበ የጥናትና ምርምር ተቋም ነው። ብሪጅ፣ በዋናነት በኢትዮጵያ እና በምሥራቅ አፍሪካ የልማት በይነ መንግሥታት (ኢጋድ) አባል አገራት ውስጥ ዲሞክራሲያዊ አሥተዳደር እንዲጎለብት እና ሰላም እንዲበለጽግ የሚሠራ ገለልተኛ እና ለትርፍ ያልተቋቋመ ፖሊሲ ተኮር የጥናት እና ምርምር ተቋም ነው።

## ተልዕኮ

ዲሞክራሲያዊ አሥተዳደር እና ሰላም ይጎለብት ዘንድ፣ ለፖሊሲ አወጣጥ ግብዓት የሚሆኑ፣ ተጨባጭነት ያላቸው ምርምሮችን ማድረግ እና የፖሊሲ ምክረ ሐሳቦችን ማቅረብ

## ርዕይ

በሕዝብ ተወካይ ምክር ቤቶች እና በቀጠናዊ የሰላም፣ ዲሞክራሲያዊ አሥተዳደር እና ሰዋዊ እና ቁሳዊ ልማት ላይ፣ በኢጋድ ቀጠና ተቀዳሚ የምርምር እና ፖሊሲ አመንጪ ማዕከል መሆን፤

## መሠረታዊ ዕሴቶች

- አጽንዖተ ትኩረት፦ ከፍተኛ ትኩረት የተሰሩ እና ተጨባጭነት ያላቸው ጥናት ምርምሮችን ማቅረብ፡፡
- አዲስነት፦ ለዲሞክራሲያዊ አሥተዳደር እና ሰላም ተግዳሮቶች ፈጠራዊ እና ተለዋዋጭ መፍትሔዎች የታከለባቸውን የመፍትሔ ሐሳቦች ማዋጣት
- ታማኝነት፦ ተዓማኒነት ያላቸውን የምርምር ውጤቶችን በማቅረብ ተዓማኒነትን መጠበቅ

## ግቦች

በኢትዮጵያ እና በኢጋድ ቀጠና የሚገኙ የፌዴራል እና የክልል ፓርላማዎች በሚከተሉት መንገዶች ማጠናከር

- ተጨባጭ ምርምሮችን መከወን
- የእንደራሴዎችን ብቃት ለማሳደግ የዐቅም ግንባታ ድጋፎችን ማድረግ
- ተጠያቂነትን እና ውጤታማነትን ለማረጋገጥ የሕዝብ ተወካይ ምክር ቤቶች ክንውኖችን መከታተል









# ማውጫ


የምክር ቤቱ ሕግ የማውጣት ተግባራት........... 3
የአሥፈጻሚ ተቋማት ቁጥጥር..................... 5
የፓርላማ ዲፕሎማሲ............................... 16
የእንደራሴዎቹ ጉብኝት............................. 18
እንደራሴዎቹ ስለ‘ራሳቸው በ‘ራሳቸው............ 19
የሕንዱ ሰው ውሎ................................. 21
ሹመት.............................................. 23
የብሪፎ ዳሰሳዊ ምልከታ፦ ኢትዮጵያ፣ ሕንድ እና ሞዲ
.................................................... 24

# የኢትዮጵያ እንደራሴዎች የወርኃ ታኅሣሥ ክራሞት

የኢትዮጵያ እንደራሴዎች ምክር ቤት፣ በወርኃ ታኅሣሥ የተለያዩ ሕገ-መንግሥታዊ ኃላፊነቶቹን አከናውኗል። ከእነዚኽ ዋንኛ ኃላፊነቶቹ መካከልም፣ ሕግጋት ማውጣት፣ የሥራ አሥፈፃሚ ተቋማት ሪፖርቶችን ማድመጥ፣ ፓርላመንታዊ ዲፕሎማሲ፣ የፌደራል ተቋማትን መጎብኘት እና የመስክ ጉብኝቶችን ማድረግ የወሩ የምክር ቤቱ አበይት ክንውኖች ናቸው። ከዚኽ በተጨማሪም፣ ሦሥት የፌድራሉን ሚኒስትሮች ወደ አዳራሹ ጠርቶ፣ ማብራሪያ ያስፈልጋቸዋል ባላቸው ርዕሰ-ጉዳዮች ላይ ጥያቄዎችን አንስቶ፣ የሚኒስትሮቹን ምላሾችን ሲያደምጥ፤ የሕንዱን ጠቅላይ ሚኒስትርን ታሪካዊ ንንግሮች አድምጧል። ይኽች የብሪጅ ዐስራ አንደኛ ዕትምም፣ እነዚኽን የምክር ቤቱን የታኅሣሥ ክራሞት ጨምሮ፣ የሕንዱን ጠቅላይ ሚኒስትር ንግግር ተንተርሳ ያዘጋጀችውን ዳሰሳ አክላ እንዲኽ ተጠናክራለች።

## 6ኛው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በ5ኛ ዓመት የሥራ ዘመን

**ታኅሣሥ 7**

### 4ኛ መደበኛ ስብሰባ

የትራንስፖርትና ሎጀስቲክስ ሚኒስትርን ማብራሪያ ማድመጥ

**ታኅሣሥ 14**

### 5ኛ መደበኛ ስብሰባ

የዕጽዋት ጥበቃ እና ኳራንታይ ረቂቅ ዐዋጅን ማጽደቅ

**ታኅሣሥ 21**

### 6ኛ መደበኛ ስብሰባ

የሥርዓተ ምኅዳር አገልግሎት ረቂቅ ዐዋጅን ማጽደቅ እና
የውጪ ጉዳይ ሚኒስትርን ማብራሪያ ማደመጥ

**ታኅሣሥ 23**

### 7ኛ መደበኛ ስብሰባ

የፍትሕ ሚኒስትርን ማብራሪያ መድመጥ

**ታኅሣሥ 27**

### 8ኛ መደበኛ ስብሰባ

ሹመቶችን ማጽደቅ

# የምክር ቤቱ ሕግ የማውጣት ተግባራት



የኢትዮጵያ የእንደራሴዎች ምክር ቤት፣ በወርኃ ታኅሣሥ ኹለት ዐዋጆችን ሲያጸድቅ፣ ወደ ቋሚ ኮሚቴዎቹ የመራቸው ምንም ዓይነት ረቂቅ ሕግጋት አልነበሩትም። ያም ሆኖ፣ በአንድ ረቂቅ ዐዋጅ ዙሪያ አንድ የአስረጂ መድረክ አካሂዷል።

## የጸደቁ ሕግጋት

የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት በወርኃ ታኅሣሥ ያጸደቀወ ቀዳሚው ረቂቅ ዐዋጅ፣ **የዕጽዋት ጥበቃ እና ኳራንታይን ረቂቅ** ዐዋጅን ነበር። የግብርና ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢው የተከበሩ ሰለሞን ላሌ ረቂቅ ዐዋጁን አስመልክቶ ቋሚ ኮሚቴው ያዘጋጀውን ሪፖርት እና የውሳኔ ሐሳብ ያቀረቡ ሲሆን፣ ረቂቅ ዐዋጁ ከጊዜ ወደ ጊዜ በፍጥነት እየተሻሻሉ እና እየተለወጡ የመጡትን ዓለም ዓቀፋዊ የዕጽዋት ጥበቃ እና ኳራንቲን ደረጃዎች እና አሠራሮች በመከተል ከዓለም ዓቀፉ ማኅበረሰብ ጋር የተናበበ ቀልጣፋ እና ውጤታማ ሥራ ለመሥራት መደላድል የሚፈጥር መሆኑን አንስተዋል ተብሏል። ሰብሳቢው አያይዘውም፣ አግባብነት ያለው እና ደረጃውን የጠበቀ የተባይ አሰሳ እና ቅኝት ሥጋት ትንተና ለማድረግ እና በመግቢያ በሮች የገቢ እና ወጭ ዕጽዋት፣ የዕጽዋት ውጤት እና ሌሎች ቁጥጥር የሚደረግባቸው ቁሳቁሶችን በተገቢው ለመቆጣጠር የሚያስችል ማዕቀፍ ያለው መሆኑን ጠቅሰዋል። እንዲኹም ዘመናዊ የተባይ መከላከል እና መቆጣጠር ሥርዓትን በመዘርጋት ምርታማነትን እና የምርት ጥራትን በማሳደግ ኢኮኖሚያዊ እና ማኅበራዊ ተጠቃሚነት በማረጋገጥ ረገድ ከፍተኛ ፋይዳ ያለው መሆኑን አስረድተዋል።

እንደራሴዎቹም፣ ፈቃድ ሳያወጡ ወይም ሕጋዊ ባልሆነ መንገድ በአየር እና በየብስ ከዕጽዋት ጋር የሚገቡ ተባዮችን ለመከላከል ዐዋጁ ያስቀመጠው የመከላከያ መንገድ ስለመኖሩ፣ ከዕጽዋት እና ከዕጽዋት ውጤቶች ጋር ተባዮች ብቻ ሳይሆኑ አረሞችም የሚገቡበት ኹኔታ ስላለ ተባይ በሚል ብቻ የተቀመጠበትን ምክንያት በተመለከተ እንዲኹም ሌሎች በርካታ ጥያቄዎች ያነሱ ሲሆን፣ በቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ ምላሽ እንደተሰጠባቸው ከምክር ቤቱ የተገኘው መረጃ ይጠቁማል። በመጨረሻም፣ እንደራሴዎቹ ይኽንኑ ረቂቅ ዐዋጅ፣ ዐዋጅ ቁጥር 1400/2018 በማድረግ በሙሉ ድምጽ አፅድቀውታል።



የግብርና ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢው የተከበሩ ሰለሞን ላሌ፤

እንደራሴዎቹ በዚኹ ወር ያጸደቁት ኹለተኛው ዐዋጅ፣ **የሥርዓተ ምኅዳር አገልግሎት ክፍያን** አስመልክቶ የቀረበላቸውን ረቂቅ ዐዋጅ ሲሆን፣ የዐዋጁን አስፈላጊነት በሚመለከትም የውኃ፣ መስኖ፣ ቆላማ አካባቢ እና አካባቢ ልማት እንዲኹም የፕላን፣ በጀት እና ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴዎች በጋራ ያዘጋጁትን ሪፖርት እና የውሳኔ ሐሳብ የቀዳሚው ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ የተከበሩ ወ/ሮ ፈቲያ አህመድ አቅርበዋል፡፡

ሥርዓተ ምኅዳሮች ዘላቂነታቸው ባልተረጋገጠ መንገድ ጥቅም ላይ እየዋሉ እና በተፈጥሮ ማገገም ከሚችሉት በላይ እየተመናመኑ የመጡ መሆኑ ብቻም ሳይሆን፣ በተለያዩ የዓለም ክፍሎች በሥርዓተ ምኅዳር አገልግሎት ዋጋ ላይ የተፈጠረው ሳይንሳዊ ግንዛቤ ማደግ ለዐዋጁ መውጣት መነሻ ምክንያት ስለመሆኑ በውሳኔ ሐሳቡ ላይ መጠቀሱ ተዘግቧል። በመሆኑም የሥርዓተ ምኅዳርን በዘላቂነት ለማሥተዳደር የሚያስችል የሥርዓተ ምኅዳር አገልግሎት ክፍያ የሕግ ማዕቀፍ እና የአሠራር ሥርዓቶችን መዘርጋት

የምክር ቤቱ አባላት በበኩላቸው የዐዋጁን አስፈላጊት በሚመለከት አስተያየት ያቀረቡ ሲሆን፣ በቀጣይ አፈፃፀም ላይ ትኩረት ሊደረግ ይገባል ያሏቸውን ሐሳቦችም ማቅረባቸውን የምክር ቤቱ መረጃ ጠቅሷቸዋል። በመጨረሻም ምክር ቤቱ የቀረበለትን ረቂቅ ዐዋጅ ቁጥር 1401/2018 አድርጎ በአንድ ድምፀ ተአቅቦ፣ በአብላጫ ድምጽ አጽድቋል፡፡



የውኃ፣ መስኖ፣ ቆላማ አካባቢ እና አካባቢ ልማትቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ የተከበሩ ወ/ሮ ፈቲያ አህመድ የውሳኔ ሀሳቡን ሲያቀርቡ፤

## አስረጂ መድረኮች

የኢትዮጵያ እንደራሴዎች፣ በዚኽ ዕትም ሽፋን በሰጠነው ወርኃ ታኅሣሥ ያካሄዱት ብቸኛው የአስረጂ መድረክ፣ **በዓለም ዓቀፍ የሕግ ትብብር ረቂቅ ዐዋጆች** ዙሪያ እንደነበር ያገኘነው መረጃ ይጠቁማል። ይኽንኑ የአስረጂ መድረክ ያካሄደው በምክር ቤቱ የሕግ እና ፍትሕ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሲሆን፣ የሥምምነቶቹ ዐዋጆች፣ ኢትዮጵያ ፍርደኞችን ለማስተላለፍ ከቻይና፣ ብራዚል እና ደቡብ አፍሪካ ጋር ያደረገቻቸው ትብብሮች እና በተመሣሣይ በኢትዮጵያ እና በቻይና መንግሥታት መካከል የተደረገው የወንጀል ጉዳዮች የጋራ የሕግ ትብብር ረቂቅ ዐዋጆች እንደሆኑ ተገልጿል።

እነዚኽ ረቂቅ ዐዋጆች ፋይዳቸው ወንጀልን ከመከላከል በላይ ነው ያሉት የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ ወ/ሮ ዕፀገነት መንግስቱ፣ የኹለትዮሽ ሥምምነቱን የሚፈርሙት የብሪክስ አባል አገራት በመሆናቸው ዐዋጆቹ ብዙ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ እና ስትራቴጂካዊ ትብብርን የሚያጠናክሩ እንደሆኑ አብራርተዋል ተብሏል። የሞት ፍርድ ከተፈረደባቸው ወንጀለኞች በስተቀር ፍርደኞችን አሳልፈው የሚሰጡ አገራት የወሰኑትን ውሳኔ በ'የአገራቸው ለማስፈፀም የሚደረጉ ሥምምነቶች እንደሆኑ የጠቆሙት ሰብሳቢዋ፣ ከኹለቱ አገራት ስምምነት ውጭ ሌላ አዲስ ውሳኔ የሚወሰንበት እና ቅጣቱን የመጨመርም ይሁን የመቀነስ ሕጋዊ መሠረት እንደሌለው ገልፀዋል ተብሏል። ይኽም ለፍርደኞቹ ቤተሰብ እንዲጎበኟቸው፣ በአገራቸው የአመጋገብ ሁኔታ እንዲመገቡ እና ከቋንቋ እና ከሌሎች ጉዳዮች ጋር ተያያዥ የሆኑ በደሎች እንዳይደርስባቸው ያደርጋሉ ማለታቸውንም መረጃው ጠቅሷቸዋል።

በአስረጂ መድረኩ ላይ የተገኙት የፍትሕ ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታው በላይሁን ይርጋ በበኩላቸው፣ አገራት በሰጥቶ መቀበል መርህ በኹለቱም ወገን የአገራቸውን ጥቅም የሚያስከብሩባቸው ስምምነቶች እንደሚሆኑ አመላክተዋል። የፖለቲካ ወንጀለኞችን አሳልፎ መስጠት ግን ዓለማ ዓቀፋዊ ስምምነቶችም አይፈቅዱም ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፣ ከሽብርተኝነት ጋር የተገናኘ ከሆነ ግን በስምምነቶቹ መሠረት ማስተላለፍ እንደሚቻል መግለጻቸው ተሰምቷል። እንደ ምክር ቤቱ መረጃ ከሆነም፣ በረቂቅ ዐዋጆች ላይ የቋሚ ኮሚቴው አባላት እና በምክር ቤቱ የሕግ ባለሙያዎች ጥያቄ እና አስተያየቶች አቀርበው ሰፊ ውይይት ተደርጎባቸዋል ተብሏል።



የሕግ እና ፍትሕ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ የተከበሩ ወ/ሮ ዕፀገነት መንግስቱ እና የፍትሕ ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታው በላይሁን ይርጋ፤

# የአሥፈጻሚ ተቋማት ቁጥጥር

የኢፌዴሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንደራሴዎች፣ ከዋና ዋና ሥራዎቻቸው አንዱ የሆነው የአሥፈጻሚ ተቋማት ቁጥጥር ሲሆን፤ በዚኽ ረገድም፣ በዚኽ ዕትም ሽፋን በሰጠነው ወርኃ ታኅሣሥ ሦሥት የፌደራል መንግሥቱን ሚኒስትሮች ወደ አዳራሹ ጠርቶ ያሳስቡኛል ባላቸው ወቅታዊ ርዕሰ-ጉዳዮች ዙሪያ ጥያቄዎችን አቅርቦ ማብራሪያዎችን አድምጧል። ከዚኽ ባለፈም፣ የአምስት ተቋማትን ከሦሥት እስከ አራት ወራት የደረሰ የ2018 በጀት ዓመት አፈጻጸምን ሲገመግም፣ ሰፊ ሊባል የሚችል የተቋማት እና የመስክ ጉብኝቶችንም አድርጓል።

## የተቋማት ሪፖርቶች

በወሩ የጊዜ ምጣኔ፣ በቀዳሚነት ወደ እንደራሴዎቹ ምክር ቤት ደርሰው የሚኒስቴር መሥሪያ ቤታቸውን አኹናዊ ኹኔታ ተጠይቀው ያብራሩት፣ **የትራንስፖርት እና ሎጀስቲክስ ሚኒስትሩ** ነበሩ። ታኅሣሥ 7 በዋለው 4ኛው መደበኛ ስብሰባ ላይ ለተገኙት ሚኒስትሩ የተከበሩ ዶ.ር. አለሙ ስሜ፣ እንደራሴዎቹ የተለያዩ ጥያቄዎችን አንስተውላቸው ነበር። ከተነሱት ጥያቄዎች መካከል፣ አደጋን ለመቀነስ እየተሰሩ ያሉ ሥራዎችን፣ የተሳፋሪ ደህንነትን እና ከታሪፍ በላይ ማስከፈልን፣ ዘርፉን በቴክኖሎጂ የማዘመን ሥራን እና በተለያዩ አካባቢዎች የአየር መንገድ ግንባታ ሥራዎችን የተመለከቱት ዋንኞቹ ነበሩ ተብሏል።

ሚኒስትሩ አለሙ ስሜም፣ አደጋዎችን ለመቀነስ የአሽከርካሪዎችን ብቃት የማረጋገጥ እና የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች እየተሰሩ መሆናቸውን ከመጥቀሳቸው ባለፈ፣ በትራንስፖርት ዘርፉ የሚስተዋሉ ችግሮችን በመቅረፍ ዘርፉን የበለጠ ለማዘመን በትኩረት እየተሠራ መሆኑን አብራርተዋል ተብሏል። የተጀመሩ አየር መንገዶችን በተመለከተም፣ በአገሪቱ የተለያዩ ክልሎች የአየር ማረፊያዎች ግንባታቸው የተጀመረው በክልል መንግስታት እና በባለሀብቶች መሆናቸውን ገልጸው፣ ግንባታቸው ደረጃቸውን የጠበቁ እንዲሆኑ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የቴክኒክ ድጋፍ እያደረገላቸው መሆኑን ተናግረዋል። ከዚኽ በተጨማሪም፣ ሕገ-ወጥ ኬላዎች በአገር ኢኮኖሚ እድገት እና ሁለንተናዊ እንቅስቃሴ ላይ የሚያሳድሩት አሉታዊ ተጽዕኖ ተገምግሞ ቁጥጥር በማድረግ፣ አሁን ላይ ቁጥራቸው እየቀነሰ መሆኑን ያነሱት ዶ.ር. አለሙ፣ ሕገ-ወጥ ኬላዎችን የማስወገድ ሥራው ተጠናክሮ የሚቀጥል መሆኑን ተናግረዋል ተብሏል። አዲሱ የተሽከርካሪ ሰሌዳ ታርጋ እየተለየ የሚፈጸመውን አድሎአዊ አሠራርን ጨምሮ በርካታ ችግሮችን የሚፈታ እንደሆነም ሚኒስትሩ ለእንደራሴዎቹ ነግረዋቸዋል።



የትራንስፖርት እና ሎጀስቲክስ ሚኒስትሩ የተከበሩ ዶ.ር. አለሙ ስሜ ማብራሪያቸውን ሲሰጡ፤

በዚኹ ወር በተካሄደው 7ኛው መደበኛ ስብሰባ ላይ የተገኙት **የፍትሕ ሚኒስትሯ ሐና አርአያ ሥላሴም**፣ በዕለቱ ከእንደራሴዎቹ ለተነሱላቸው የተለያዩ ጥያቄዎች ማብራሪያዎችን ሰጥዋል። የሕግ የበላይነትን በማስጠበቅ የዜጎች መብቶች እንዲከበሩ እየተሠራ መሆኑን ሲናገሩ የተደመጡት ሚኒስትሯ፣ ለዚኽም በየደረጃው የማሻሻያ ሥራዎች መተግበራቸውን አንስተዋል።

የዜጎችን የዲሞክራሲያ እና የሰብዓዊ መብት ጥያቄዎችን በተመለከተ ማንኛውም አካል የመብት ጥያቄ ሲኖረው ሕገ መንግሥቱን እና የአገሪቷን ሕጎችን ባከበረ መንገድ ሊያቀርብ ይገባል ያሉት ወ/ሮ ሐና፣ ከሕግ ውጭ የሆኑ ጉዳዮች ሲኖሩ ግን በየደረጃው ተጠያቂነት እንደሚኖርም አብራርተዋል ተብሏል። ከፍትሕ አገልግሎት አሰጣጥ እና ከወንጀል ጋር የተያያዙ ጉዳዮች ጋር በተገናኘ ለተነሱ የአገልግሎት አሰጣጥ ጥያቄዎች የወንጀል ጉዳዮች በባህሪያቸው ውስብሰብነት ያላቸው እና ዝርዝር መረጃ እና ማጣራትን የሚፈልጉ በመሆናቸው ጊዜ ሊወስዱ የሚችሉ መሆናቸውንም ጠቁመዋል፡፡ ስለሆነም የወንጀል እና የፍትሕ ጉዳዮች ዝርዝር መረጃ ማጣራትን እንደሚጠይቅ እና የማጣራቱ ሥራ ጊዜ ተወስዶ በጥንቃቄ የሚሠራ መሆኑን ከግምት ውስጥ ማስገባት ተገቢ መሆኑንም በአጽንዖት መናገራቸውን ከምክር ቤቱ የተገኘው መረጃ ጠቅሷቸዋል።



የፍትሕ ሚኒስትሯ ሐና አርአያ ሥላሴ፣ ከእንደራሴዎቹ ለተነሱላቸው ጥያቄዎች ማብራሪያ በሰጡበት ዕለት፤

በዚኹ ወርኃ ታኅሣሥ በሦሥተኛነት ወደ እንደራሴዎቹ ምክር ቤት ብቅ ያሉት **የውጪ ጉዳይ ሚኒስትሩ ዶ.ር. ጌዲዮን ጢሞቴዎስ፣** ከፐብሊክ ዲፕሎማሲ እስከ የቆንጽላ ጽሕፈት ቤት አገልግሎቶች፣ ከባሕር በር እስከ የአሰብ ወደብ የደረሱ ጥያቄዎች ከእንደራሴዎቹ በኩል ተነስቶላቸው፣ ‘ርሳቸውም የመንግሥታቸውን አቋም ሰፋ አድረገው አብራርተዋል።

የፐብሊክ ዲፕሎማሲን በተመለከተ ከሌሎች ተቋማት ጋር በመቀናጀት የተለያዩ ሥራዎች እየተከናወኑ መሆናቸውን ያነሱት ውጪ ጉዳይ ሚኒስትሩ፣ ባለፉት አምስት ወራት በማይናማር በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ የነበሩ 1 ሺህ 300 ዜጎች ወደ አገራቸው እንዲመለሱ መደረጉን ተናግረዋል። ዜጎች በውጭ አገራት መብታቸው እና ክብራቸው ተጠብቆ እንዲሠሩ የመደመር መንግስት ቁርጠኛ አቋም እንዳለውም ረገጥ አድርገው ሲናገሩ የተደመጡት ሚኒስትሩ፣ የኢትዮጵያ መንግስት ባደረገው ከፍተኛ ክትትል ባለፉት አምስት ወራት ብቻ ከማይናማር በተጨማሪ በሳዑዲ ዓረቢያ የነበሩ 26 ሺህ ዜጎችን ወደ አገራቸው እንዲመለሱ ማድረጉን ለእንደራሴዎቹ ነግረዋቸዋል። ዜጎች ለሕይወት አስጊ ከሆኑ ሕገ-ወጥ ጉዞዎች ሊታቀቡ እንደሚገባ ያሳሰቡት ዶ.ር. ጌዲዮን፣ ኢትዮጵያውያን በሕጋዊ መንገድ ወደ ውጭ ሄደው እንዲሠሩ ከሥራ እና ክህሎት ሚኒስቴር ጋር በቅንጅት እየተሠራ መሆኑን አስረድተዋል። በተለይም በአረብ አገራት በሚገኙ ቆንስላዎች ዜጎችን የሚከታተሉ ዲፕሎማቶች ተመድበው የቅርብ ክትትል እየተደረገ መሆኑንም አመላክተዋል ተብሏል።

በባሕር በር ጥያቄ ጉዳይ ከእንደራሴዎቹ ለተነሳላቸው ጥያቄም፣ ኢትዮጵያ ያቀረበችው የባሕር በር ጥያቄ የመንግስት ወይም የአንድ ፓርቲ ጥያቄ ብቻ ሳይሆን ትውልድ ተሻጋሪ ግብ ያለው የትውልድ ጥያቄ እንደሆነ ያነሱት ሚንስትር ጌዲዮን፣ የኢትዮጵያን የባሕር በር ባለቤትነት ለማረጋገጥ ሚንስቴር መሥሪያ ቤቱን ጨምሮ የተለያዩ ኢትዮጵያውያን እና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ከፍተኛ ሥራ እያከናወኑ መሆኑንም አብራርተዋል። በተለያዩ አገራት የሚገኙ የኢትዮጵያ ኤምባሲዎችም የአገሪቱን የባሕር በር ፍላጎት ለማሳካት እያከናወኑት ያለው ተግባር አበረታች እንደሆነም አክለው የጠቀሱት ዶ.ር. ጌዲዮን፣ በቀጣይም የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅም ለማስከበር በሚደረገው ዲፕሎማሲያዊ ጥረት ሁሉም ዜጋ የሚጠበቅበትን ኃላፊነት ሊወጣ እንደሚገባ ጠቁመዋል ተብሏል።



የውጪ ጉዳይ ሚኒስትሩ ዶ.ር. ጌዲዮን ጢሞቲዎስ፣ ማብራሪያ በሰጡበት ዕለት፤

የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት፣ ባሳለፍነው ታኅሣሥ ወር፣ ከሦሥቱ ሚኒስትሮች ባለፈ የሌሎች የፌደራል ተቋማትን የ2018 በጀት ዓመት የሥራ አፈጻጸም ሲገመግም፣ በጊዜ ቅደም ተከተል ቀደብ ብሎ የገመገመው **የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ባለሥልጣንን** የ2018 በጀት ዓመት የአንደኛ ሩብ ዓመት ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርትን ነበር።

ሪፖርቱን የገመገመው በምክር ቤቱ የከተማ መሠረተ ልማት እና ትራንስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሲሆን፣ የኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ ፕሮፌሰር መሀመድ አብዱ፣ ባለሥልጣኑ በፕሮጀክቶች አፈፃፀም የሚስተዋሉ ችግሮችን በጥናት ላይ ተመስርቶ ለመፍታት ትኩረት ሰጥቶ መሥራት እንዳለበት አቅጣጫ ሰጥተዋል ተብሏል። የፕሮጀክቶችን አፈጻጸም ለማሻሻል የኮንትራክተሮችን እና የአማካሪዎችን አቅም ማሳደግ ይገባል ያሉት ሰብሳቢው፣ በብሔራዊ ቲያትር ፕሮጀክት የመጣውን ለውጥ በሌሎች ፕሮጀክቶች ላይም ሊታይ እንደሚገባ አመላክተዋል።

የቋሚ ኮሚቴው ምክትል ሰብሳቢ የተከበሩ ዶ.ር. እሸቱ ተመስገን በበኩላቸው፣ በኮንስትራክሽን ዘርፉ የሕዝብ እና የመንግስትን ሀብት ከብክነት ለመቆጣጠር የመሠረተ ልማት ደህንነቶች ላይ አጠናክሮ መሥራት እንደሚገባ ማሳሰባቸው ተጠቅሷል። የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ባለሥልጣን ዋና ዳይሬክተር ዶ.ር. መስፍን ነገዎ በበኩላቸው፣ ባለሥልጣም መሥሪያ ቤቱ በበጀት ዓመቱ 300 ፕሮጀክቶች ላይ ቁጥጥር ለማድረግ አቅዶ በየሩብ ዓመቱ ከፋፍሎ እየሠራ መሆኑን ገልጸው፣ በፕሮጀክቶች ክትትል እና ቁጥጥር በማድረግ ግብረ መልስ እየተሰጠ መሆኑን ለቋሚ ኮሚቴው አባላት አብራርተዋል፡፡ የዩኒቨርሲቲ ፕሮጀክቶች አፈጻጸም ላይ ተጠያቂነትን ከማረጋገጥ አንጻር በሚመለከተው አካል የማስፈጸም አቅምን ያማከለ እርምጃ የተወሰደ መሆኑንም ጨምረው ማብራራታቸውን የምክር ቤቱ መረጃ ያሳያል።



የከተማ መሠረተ ልማት እና ትራንስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አባላት፣ የኮንስትራክሽን ባለሥልጣኑን ሪፖርት

የወሩ ኹለተኛ የዚኹ በጀት ዓመት የሦሥት ወራት የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት አቅራቢ የነበረው **የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ** ሲሆን፣ የተቋሙን ሪፖርትም በምክር ቤቱ የዲሞክራሲ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ገምግሟል ተብሏል። የቦርዱን የሩብ ዓመት አፈፃፀም ሪፖርት እና የ7ኛው ጠቅላላ ምርጫ የቅድመ ዝግጅት ተግባራትን ለቋሚ ኮሚቴው ያቀረቡት የቦርዱ ሰብሳቢ ወ/ሮ ሜላትወርቅ ኃይሉ ሲሆኑ፣ የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ እውነቱ አለነ፣ ቦርዱ ለቀጣዩ ጠቅላላ ምርጫ እያደረገ ያለው ቅድመ ዝግጅት አበረታች መሆኑን ገልጸዋል ተብሏል።

ከዚኽ ባለፈም፣ የመራጮች እና የዕጩዎች ምዝገባን ዲጂታላይዝ በሆነ መንገድ ለማከናወን የተጀመሩ ሥራዎች ተጠናክረው እንዲቀጥሉ ያሳሰቡት ሰብሳቢው፣ የበለፀጉትን ቴክኖሎጂዎች ደህንነት እና ብቃት መፈተሸ እንደሚገባው አሳስበዋል። የቋሚ ኮሚቴው ምክትል ሰብሳቢ የተከበሩ አዝመራ አንደሞ በበኩላቸው፣ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የቀጣዩን አገራዊ ምርጫ ለማሳካት ያከናወናቸው ተግባራት ተስፋ ሰጪ መሆናቸውን አመላክተዋል ተብሏል።

የቦርዱ ሰብሳቢ ወ/ሮ ሜላትወርቅ ኃይሉ፣ ተጨማሪ የምርጫ ጽሕፈት ቤቶችን የማደራጀት እና በሰው ኃይል የማጠናከር ሥራ እንደተከናወነ፣ የተሟላ መሠረተ ልማት የተሟላባቸው የምርጫ ክልሎች እና ጣቢያዎች የዕጩ እና መራጮች ምዝገባ በቴክኖሎጂ እንደሚታገዝ፣ አጠቃላይ የምርጫ አካሄድ የጊዜ ሠሌዳ ለሕዝብ ይፋ መደረጉን እና የድምጽ መስጫ ቀን ግንቦት 24 መሆኑንም ጭምር ለቋሚ ኮሚቴው አስታውቀዋል ተብሏል። የመራጮች እና የእጩዎች ምዝገባን ቦርዱ ባለማቸው ሶፍትዌሮች በመታገዝ ለማከናወን ሥራዎች እየተሰሩ መሆኑን የገለጹት ወይዘሮዋ፣ ይኽ ሙከራ በመላ አገሪቱ እያደገ እንደሚሄድ አብራርተዋል ተብሏል።



የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ሰብሳቢዋ ወ/ሮ ወ/ሮ ሜላትወርቅ ኃይሉ፣ የተቋማቸውን ሪፖርት ሲያቀርቡ፤

በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የፕላን፣ በጀት እና ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፣ **የገቢዎች ሚኒስቴርን እና የጉምሩክ ኮሚሽንን** የ2018 በጀት ዓመት የአራት ወራት ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርትን የገመገመበት የውይይት መድረክም ሌላይኛው የወሩ የሥራ አሥፈጻሚ ቁጥጥር ክንውኑ ነበር። የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ ደሳለኝ ወዳጄ በስብሰባው መክፈቻ በሰጡት አስተያየት፣ በሕገ-መንግሥቱ በተሰጠው ክትትል እና ቁጥጥር የማድረግ ኃላፊነት የዛሬው የውይይት መድረክ መዘጋጀቱን ጠቁመው፣ የገቢዎች ሚኒስትሯ ወይዘሮ ዓይናለም ንጉሴ፣ የመሥሪያ ቤታቸውን የአራት ወራት የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት እንዲያቀርቡ መድረኩን ክፍት አድርገዋል፡፡

የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ ደሳለኝ ወዳጄ በሰጡት አስተያየት፣ የገቢዎች ሚኒስቴር እና የጉምሩክ ኮሚሽን የገቢ አሰባሰብ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻለ መምጣቱን ጠቁመው፣ የታክስ አጭበርባሪዎችን እና ኮንትሮባንድን ለመከላከል እና አገልግሎትን ለማሻሻል ቴክኖሎጂን መጠቀም አስፈላጊ መሆኑን አስገንዝበዋል፡ ፡ ሰብሳቢው አክለውም መሥሪያ ቤቶቹ የፌዴራል ዋና ኦዲተር የኦዲት ግኝትን ለማስተካከል የዕቅዳቸው አካል አድርገው መሥራት እንዳለባቸውም ተናግረዋል ተብሏል።

የቋሚ ኮሚቴው ምክትል ሰብሳቢ ዶ.ር. አብርሃም አለማየሁ በበኩላቸው፣ ቋሚ ኮሚቴው በየሩብ ዓመቱ የሚሰጠው ግብረ መልስ የዕቅዳቸው አካል አድርገው በመሥራታቸው ጥሩ ውጤት እየተመዘገበ በመሆኑ ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት ተናግረዋል ተብሏል፡፡ የገቢዎች ሚኒስትሯ ዓይናለም ንጉሤ፣ የመሥሪያ ቤታቸውን የአራት ወራት የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ባቀረቡበት ወቅት፣ የ2018 በጀት ዓመት የገቢ ዕቅድ አፈጻጸም ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻለ በመምጣቱ የዚህ በጀት ዓመት የገቢ አሰባሰብም ጤናማ መሆኑን ተናግረዋል ተብሏል፡፡ ከዚያ ባለፈም ሚኒስትሯ፣ ቋሚ ኮሚቴው በየሩብ ዓመቱ የሚሰጠውን ግብረ መልስ እና የፌዴራል ዋና ኦዲተርን የኦዲት ግኝት የእቅድ አካል አድርገው በመሥራታቸው የመሥሪያ ቤታቸው የገቢ አሰባሰብ እየተሻሻለ መምጣቱን መናገራቸው ተዘግቧል።



የፕላን፣ በጀት እና ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢው ደሳለኝ ወዳጄ፤

**የኢትዮጵያ መንገዶች አሥተዳደር** በአገሪቱ በተለያዩ አከባቢዎች በመገንባት ላይ የሚገኙ የመንገድ መሠረተ ልማት ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው ጊዜ እና ጥራት ለመፈጸም የሚያስችሉ አዳዲስ የገቢ ማመንጨት ስልቶችን ነድፎ መሥራት እንዳለበት፣ በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የከተማ መሠረተ ልማት እና ትራንስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ያሳሰበበት ኩነትም፣ አንዱ የወርኃ ታኅሣሥ የሥራ አሥፈጻሚ ቁጥጥር ክንውን ነበር።

የኢትዮጵያ መንገዶች አሥተዳደር የ2018 በጀት የ1ኛ ሩብ ዓመት እቅድ አፈፃፀም ሪፖርት በገመገመበት ወቅት፣ የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ ፕሮፌሰር መሀመድ አብዶ፣ በግንባታ ሂደት ላይ ያሉ ፕሮጀክቶችን ለማጠናቀቅ ከአንድ ነጥብ ሶስት ትሪሊዮን ብር በላይ እንደሚጠይቅ አንስተዋል። ከዚኽ ባለፈም፣ የመንገድ ግንባታ ፕሮጀክቶች በአምስት ዓመት እና ከዛ በታች ለማጠናቀቅ የሚያግዝ እና ተቋሙ የተለየ የገቢ ማመንጫ ስልቶችን ቀይሶ በማጥናት ላይ የተመሠረተ ሥራ መሠራት እንዳለበት ሰብሳቢው አስገንዝበዋል ተብሏል።

በተያዘው በጀት ዓመት መንግስት ለኢትዮጵያ መንገዶች አሥተዳደር የመደበው አንድ መቶ ስምንት ቢልዮን ብር መሆኑን ያስታወሱት ሰብሳቢው፣ በቀጣይ ዓመታት በዚህ የበጀት አቅም ፕሮጀክቶችን ለማጠናቀቅ ከተፈለገ በትንሹ ከዐሥር ዓመት በላይ እንደሚፈልጉም አመላክተዋል። የቋሚ ኮሚቴው ምክትል ሰብሳቢ የተከበሩ ዶ.ር. እሸቱ ተመስገን በበኩላቸው፣ የኢትዮጵያ መንገዶች አሥተዳደር የፕሮጀክቶችን የግንባታ አፈጻጸም ለማሳደግ እንዲረዳው ተቋማዊ አሠራሩን በቴክኖሎጂ መዘመን እና ከሰው ንክኪ ነፃ የሚሆኑበትን የአሠራር ስልቶችን መከተል እንዳለበት አሳስበዋል ተብሏል።

የኢትዮጵያ መንገዶች አሥተዳደር ዋና ዳይሬክተሩ ኢንጂነር መሀመድ አብዱልራህማን በበኩላቸው፣ በአንዳንድ የፕሮጀክት ግንባታ ባለባቸው አካባቢዎች ላይ ያለ የፀጥታ ችግር፣ ግንበታዎች በተያዘላቸው ጊዜ እንዳይጠናቀቁ ተግዳሮት እንደሆነባቸው አስረድተዋል፡፡ የጥሬ ገንዘብ እጥረት እና ውዝፍ የካሳ ክፍያዎች በወቅቱ ባለመከፈላቸው ምክንያት በፕሮጀክቶች የግንባታ አፈፃፀም ላይ ጫና እያሳደረ መሆኑንም ዋና ዳይሬክተሩ አያይዘው መጥቀሳቸውን ከምክር ቤቱ የተገኘው መረጃ ይጠቁማል።



የኢትዮጵያ መንገዶች አሥተዳደር ዋና ዳይሬክተሩ ኢንጂነር መሀመድ አብዱልራህማን፣ የተቋማቸውን ሪፖርት ሲያቀርቡ፤

# የተቋማት እና የመስክ ጉብኝቶች

የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት፣ በመስከረም ወር የተጠቀሱትን ሚኒስትሮች ማብራሪያ ማድመጥ እና የተጠቀሱትን ተቋማት ሪፖርቶች መገምገም ብቻም ሳይሆን፣ በ'የቋሚ ኮሚቴዎቹ በኩል ከሃያ ያላነሱ ተቋማትን ሲጎበኝ፣ ከጋምቤላ እስከ ድሬ ዳዋ፣ ከኦሮሚያ እስከ ሲዳማ፣ ከሐረር እስከ ማዕከላዊ ኢትዮጵያ እና ቤኒሻንጉል ጉምዝ ያሉት ክልሎችም በዚኽ ወር የመስክ ጉብኝት ዕጣ የደረሳቸው ሆነዋል።

## የተቋማቱ ጉብኝቶች

በወርኃ ታኅሣሥ አጋማሽ በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የሰው ሀብት ልማት፣ ሥራ ስምሪት እና ቴክኖሎጂ ጉዳዮች ቋሚ ኮሜቴ የተጎበኘው **የሥራ እና ክህሎት ሚኒስቴር** አንዱ የተጎበኘ ተቋማት ማሳያ ነበር። የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ ዶ.ር. ነገሪ ሌንጮ፣ በተቋሙ አመራሮች እና ሠራተኞች መካከል ያለው ግንኙነት እና ቅንጅታዊ አሠራር እንዲኹም ዕቅድ እና ሪፖርት በጋራ ስለመገምገሙ እና አቅጣጫ ስለመቀመጡ አንስተዋል ተብሏል። ወደ ውጭ አገር ለሥራ የሚሄዱ ዜጎች ሕጋዊነቱን ጠብቀው እንዲሄዱ እና ዜጎች በሚሰሩባቸው አገራት ደህንነት እና ተጠቃሚነታቸው የተጠበቀ መሆኑን ክትትልና ድጋፍ መደረጉን ለማረጋገጥ ነው ብለዋል።

የሥራ ዕድል ፈጠራን በተመለከተ ያለውን አገራዊ ከፍተኛ የሥራ እድል ፍላጎት ለማሟላት በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በኩል ምን የተለየ ስትራቴጂ ተቀይሶ እየተሠራ ስለመሆኑም ሰብሳቢው ማንሳታቸው ተዘግቧል። የሥራ እና ክህሎት ሚኒስቴር ሚኒስትሯ ክብርት ሙፈሪሃት ካሚል፣ ቋሚ ኮሚቴው ለሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ክትትል እና ቁጥጥር ለማድረግ ትልቅ አበርክቶ አድርጓል ብለዋል።

ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ከክልል፣ ከተጠሪ ተቋማት እና ከባለድርሻ አካላት ጋር በጋራ በመሆን የምክክር መድረክ እንዳደረገ ያነሱት ሚኒስትሯ፣ ከክህሎት ልማት አኳያ በበጀት ዓመቱ አዲስ ተማሪዎችን የቅበላ ሥራ የሳይኮሜትሪክ ምዘናን መሰረት በማድረግ እንደተሠራም ጠቁመዋል ተብሏል። የቋሚ ኮሚቴው ምክትል ሰብሳቢ የተከበሩ ዶክተር ቤተልሔም ላቀው በበኩላቸው፣ ከቴክኒክ እና ሙያ ሥልጠና ጋር በተያያዘ የኅብረተሰቡን ግንዛቤ ለማሳደግ የክረምት መረሃ ግብሮችን በተከታታይ በመተግበር ገጽታውን ለማሻሻል በልዩ ትኩረት ሊሠራ እንደሚገባ አመላክተዋል።


የሥራ እና ክህሎት ሚኒስቴር ሚኒስትሯ ሙፈሪሃት ካሚል በተቋማቸው የመስክ ጉብኝት ወቅት፤

ሌላይኛው የወሩ ተጎብኚ ማሳያ ተቋም፣ **የኢትዮጵያ ብሮድ ካስቲንግ ኮርፖሬሽን** ሲሆን፣ ጎብኚውም በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የዴሞክራሲ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ነበር ተብሏል። የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ እውነቱ አለነ፣ የኢትዮጵያ ብሮድ ካስቲንግ ኮርፖሬሽን ከለውጡ በፊት አድማጭ እና ተመልካች ያጣ እና ውድቀት የተጋረጠበት ተቋም እንደነበር ገልጸው፣ አኹን ላይ መሠረታዊ ችግሮች ተፈተው ተጨባጭ ውጤቶችን እያስመዘገበ እንደሚገኝ መረጋገጡን አስገንዝበዋል ተብሏል። ከዚያ ባለፈም፣ ተቋሙ የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅም በማስጠበቅ፣ አገራዊ አንድነትን በማጠናከር እና የጋራ ትርክትን በማቀንቀን ረገድ የጀመራቸውን ሥራዎች የበለጠ አጠናክሮ ሊቀጥል እንደሚገባ አመላክተዋል።

የቋሚ ኮሚቴው ምክትል ሰብሳቢ የተከበሩ አዝመራ አንዴሞ በበኩላቸው፣ ተቋሙ ከጊዜ ወደ ጊዜ ለውጦችን እያስመዘገበ መሆኑን ገልጸው፣ የኢትዮጵያን ብልጽግና እውን ለማድረግ በወል ትርክት ላይ ትኩረት የማድረግ የተቋሙ ዋና ሥራ መሆኑን ማስገንዘባቸው ተጠቁሟል። የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን ዋና ሥራ አሥፈጻሚ አቶ ቢኒያም ኤሮ በበኩላቸው፣ በተቋሙ የነበሩ ዘርፈ ብዙ ችግሮችን ለማስተካል በተደረጉ የማሻሻያ ሥራዎች አመርቂ ለውጦች እየታዩ መሆናቸውን ለቋሚ ኮሚቴው ገልጸዋል። የኮርፖሬሽኑ ምክትል ሥራ አሥፈፃሚ እና የሚዲያ ዘርፍ ኃላፊው ዘላለም እንደሻው በተራቸው፣ ተቋሙ ለአገራዊ አንድነት፣ ለብሔራዊ ትርክት እና ለኢትዮጵያ ብልጽግና መሳካት የበኩሉን ድርሻ ለመወጣት በትኩረት እየሠራ መሆኑን ተናግረዋል ተብሏል።



የዴሞክራሲ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢው የተከበሩ አውነቱ አለነ፤

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት፣ በዚኹ ወር ከተጎበኙት ተቋማት መካከል ለማሳያ ሊጠቀስ የሚችለው ነው። ተቋሙን የጎበኙት በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የመንግስት የልማት ድርጅቶች ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አባላት ሲሆኑ፣ የኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ መለሰ መና፣ የመስክ ምልከታው አላማ ተቋሙ አሁን ያለበትን ደረጃ በቦታው ተገኝቶ በመገምገም የተገኙ ጠንካራ እና ደካማ እንዲኹም ትኩረት የሚሹ ጉዳዮችን በመለየት ግብረ መልስ ለመስጠት እንደሆነ ጠቁመዋል ተብሏል። እንደ ምክር ቤቱ መረጃ ከሆነም፣ ትኩረት ከሚደረግባቸው ጉዳዮች ውስጥ የተቋሙ ትርፋማነት፣ ለሠራተኛው እና ለደንበኞች የተቋሙ የሥራ አካባቢ ምቹነት፣ ለሠራተኛው ግብዓት ከማሟላት አኳያ ሠራተኛው የሚያነሳቸውን ጉዳዮች በዴሞክራሲያዊ እና በውይይት የሚፈታበት አግባብ የሚሉት ይገኙበታል ተብሏል።



የመንግስት የልማት ድርጅቶች ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አባላት፣
የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎትን በጎበኙበት ወቅት፤

እንደራሴዎቹ፣ በወርኃ ታኅሣሥ **የኢትዮጵያ ልማት ባንክንም** በምክር ቤቱ የመንግስት ልማት ድርጅቶች ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በኩል ጎብኝተው እንደነበር መረጃው ያሳይል። የቋሚ ኮሚቴው አባል እና የምልከታ ቡድኑ መሪ የተከበሩ ኢያሱ ሳላ፣ የኢትዮጵያ ልማት ባንክ እንደሁልጊዜው ዘርፈ ብዙ ሥራዎችን ለአገር እያበረከተ መሆኑን በምልከታቸው ተናግረዋል።

ቋሚ ኮሚቴው፣ በባንኩ የሚደገፉ ኹለት ፋብሪካዎችን ጎብኝቶ ከባቱ ቅርንጫፍ ኃላፊዎች ጋርም ውይይት አድርጓል ተብሏል። በተያያዘም ቋሚ ኮሚቴው በኢትዮጵያ ልማት ባንክ ባቱ ቅርጫፍ ተገኝቶ የቅርንጫፉን ሠራተኞች እና ኃላፊዎችን በተናጥል አወያይቷል። የተቋሙ ሠራተኞችም የተለያዩ የዝውውር፣ የኦዲት አሠራር፣ የእድገት እንዲኹም የንብረት አወጋገድ ተግዳሮቶችን ለቋሚ ኮሚቴው አቅርበዋል ተብሏል። የምልከታው ቡድኑ መሪ የተከበሩ ኢያሱ ሳላ፣ ቅርንጫፉ ባቀረበው ሪፖርት መሰረት ምንም አይነት የተበላሸ ብድር አለመኖሩን በጥንካሬ መግለጻቸው ተዘግቧል። በሌላ በኩል፣ የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው የግዥ ሥርዓቱን አጥርቷል ያሉት የተከበሩ ኢያሱ፣ በዚህ መሰረት ቅርንጫፉ የግዥ እና ንብረት አወጋገድ ሥርዓቱን መቃኘት እንዳለበት አመላክተዋል ተብሏል።



የመንግስት ልማት ድርጅቶች ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አባላት፣
የኢትዮጵያ ልማት ባንክን በጎበኙበት ወቅት፤

በወሩ ከተጎበኙት ተቋማት መካከል የመጨረሻ ማሳያ ሊሆን የሚችለው፣ በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የውጭ ግንኙነት እና የሰላም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የተጎበኘው **ሁርሶ ኮንተንጀንት ወታደራዊ ማሠልጠኛ ትምህርት ቤት** ነው። የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ ዶ.ር. ዲማ ነጎ፣ የመስክ ምልከታው ዓላማ ትምህርት ቤቱ አገርን እና ሕገ-መንግስታዊ ሥርዓቱን ከወራሪ ኃይሎች እና ከፀረ ሰላም ቡድኖች መጠበቅ የሚችሉ ብቁ የመከላከያ ሠራዊት አባላትን ለማፍራት እያከናወነ የሚገኘውን የማስተማር እና የሥልጠና ሂደት ለመመልከት ያለመ ነው ብለዋል ተብሏል፡፡

የትምህርት ቤቱ ዋና ኃላፊ ብርጋዴር ጄነራል አዲሱ ተርፋሳ በበኩላቸው፣ ትምህርት ቤቱ የአገርን ሰላም እና አንድነት የሚያስጠብቁ እና በተለያዩ ዓለም ዓቀፍ የሰላም ማስከበር ግዳጆች የሚሰማሩ የሰላም አስከባሪ ሠራዊት አባላትን በብቃት በማሠልጠን ላይ እንደሚገኝ ተናግረዋል፡፡ ጄኔራሉ አክለውም፣ ትምህርት ቤት ዘመኑ የሚጠይቀውን የቴክኖሎጂ ዕውቀት መሰረት በማድረግ ትምህርት ቤቱ ለበርካታ እጩ የጦር መኮንኖች በተግባር የተደገፈ ሥልጠና በመስጠት ላይ እንደሚገኝም ገልጸዋል።

የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ ዲማ ነጎ፣ የጦር ትምህርት ቤቱ ከክልል እና ከከተማ መሥተዳደር የጸጥታ እና የደኅንነት አካላት ጋር ያለውን ቅንጅታዊ አሠራር አጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት አመላክተዋል። ትምህርት ቤቱ ከተሰጠው ተልዕኮ ጎን ለጎን፣ በግብርና ሥራዎች፣ በመንገድ ግንባታ፣ ለተማሪዎች በሚደረግ ድጋፍ፣ በሰብል ስብሰባ እና መሰል የበጎ አድራጎት ሥራዎች በአካባቢው የሚገኙ የማኅበረሰብ ክፍሎችን በማገዝ ተጠቃሚ ማድረግ መቻሉንም ብርጋዴር ጄነራል አዲሱ ተርፋሳ መጥቀሳቸው ተሰምቷል።



የውጭ ግንኙነት እና የሰላም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አባላት፣ ሁርሶ ወታደራዊ ማሠልጠኛን ሲጎበኙ፤

## የመስክ ጉብኝቶች

የኢትዮጵያ እንደራሴዎች፣ በወርኃ ታኅሣሥ የመስክ ምልከታ ካደረጉባቸው ክልሎች በጊዜ ምጣኔ ቀዳሚ የሆነው **ቤኒሻንጉል ጉምዝ** ክልል ሲሆን፣ ወደ ዚያ ክልል ያመሩትም በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የውኃ፣ መስኖ፣ ቆላማ አካባቢ እና አካባቢ ልማት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አባላት ነበሩ ተብሏል። የቋሚ ኮሚቴው አባል እና የመስክ ጉብኝቱ አስተባባሪው የተከበሩ ኢንጂነር ኢብሳ ዩሱፍ፣ የቀረቡት የዕቅድ አፈፃፀሞች በተጨባጭ ምን እንደሚመስሉ እና ያላቸው ዕድገት በመስክ ምልከታው የሚረጋገጡ መሆናቸውን አስገንዘበዋል። የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ምክር ቤት አፈ-ጉባኤ የተከበሩ አስካል አልበሮ፣ ክልሉ በሚጠበቀው የለውጥ ጎዳና ላይ እንዲጎዝ የቋሚ ኮሚቴው የመስክ ጉብኝት በተጨባጭ ለመገምገም እያደረገ ያለው የክትትል እና የቁጥጥር ሥራ ለክልሉ መሠረታዊ ለውጥ አስተዋጽኦው ቀላል እንዳልሆነ ገልጸዋል ተብሏል።



የውኃ፣ መስኖ፣ ቆላማ አካባቢ እና አካባቢ ልማት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አባላት በቤኒሻንጉል ጉብኝት ወቅት፤

ድንበርተኛዋ የኢትዮጵያ ክልል የሆነችው **ጋምቤላም፣** በእንደራሴዎቹ ከተጎበኙት ክልሎች መካከል የወሩ ማሳያ ሆናለች። ወደ ክልሏ የደረሱት በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የኢንዱስትሪ እና ማዕድን ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፣ በክልሉ አቦቦ ወረዳ በልዩ አነስተኛ እና በባህላዊ ወርቅ ምርት የተሰማሩ ማኅበራትን የሥራ እንቅስቃሴ ተመልክቷል።

ወርቅ በባህላዊ እና በዘመናዊ መንገድ እንዴት ይመረታል? የግብይት ሂደቱ ሕጋዊነት ምን ይመስላል? እንዲኹም የማኅበረሰብ አገልግሎት እና በቁፋሮ የተጎዳውን መሬት መልሶ ማልማት የሚሉት በመስክ ምልከታው ትኩረት የተደረገባቸው ነጥቦች እንደነበሩም ተዘግቧል። በዚኽ መሰረት በተለይም ልዩ አነስተኛ ወርቅ አምራች ማኅበራት የሚያመርቱትን ወርቅ ወደ ብሔራዊ ባንክ ማስገባታቸው በጥንካሬ የሚታይ መሆኑን ያነሳው ቋሚ ኮሚቴው፣ በቁፋሮ የተጎዳውን መሬት መልሶ የማልማት እና የማምረት አቅምን የማሳደግ ጉዳይ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል ብሏል ተብሏል። የወረዳው አመራሮች በበኩላቸው ኮንትሮባንድን ለመከላከል የሚያስችሉ ተግባራትን እያከናወኑ መሆኑን እና ድርጅቶቹ የተጎዳውን መሬት መልሰው እንዲያለሙ በማድረግ ረገድ ትኩረት ሰጥተው እየሰሩ መሆኑን ለቋሚ ኮሚቴው አባላት ገልጸውላቸዋል ተብሏል። ማኅበራቱ ምርታቸውን ለብሔራዊ ባንክ እንዲያስገቡም ተከታታይ የግንዛቤ ሥራ እንደሚሠራም ማስረዳታቸውን ከምክር ቤቱ የተገኘው መረጃ ይጠቁማል።



የኢንዱስትሪ እና ማዕድን ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አባላት፣ በጋምቤላ ጉብኝታቸው ወቅት፤

በዚኹ ታኅሣሥ ወር የመስክ ጉብኝት ከተደረገባቸው ክልሎች ሌላይኛዋ **ማዕከላዊ ኢትዮጵያ** ክልል ስትሆን፣ ወደዚያ አዲሱ የፌዴሬሽኑ ክልል የደረሱት በምክር ቤቱ የከተማ፣ መሠረተ ልማት እና ትራንስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አባላት መሆናቸው ተሰምቷል። ምልከታው የተጀመረው ከክልሉ ምክር ቤት ቋሚ ኮሚቴዎች ሰብሳቢዎች እና ከክልሉ የሥራ ኃላፊዎች ጋር በተደረገ የመግቢያ ውይይት ሲሆን፣ ቋሚ ኮሚቴው የክልሉ መቀመጫ በሆኑት ሆሳዕና፣ ወልቂጤ እና ቡታጅራ ከተሞች እንዲኹም የስልጤ ዞን መቀመጫ በሆነችው ወራቤ ከተማ ውስጥ የተሰሩ የመሠረተ ልማት፣ የኮሪደር እና የትራንስፖርት አገልግሎት ሥራዎችን ተዘዋውሮ ተመልክቷል ተብሏል።

ቋሚ ኮሚቴው በአራቱም ከተሞች በተደረጉ የመስክ ምልከታ ሥራዎች ለእያንዳንዳቸው ከተሞች ግብረ መልስ የሰጠ ሲሆን፣ በመስክ ምልከታው መጨረሻ የክልሉ አመራር የትኩረት መስኮችን ለይቶ መሥራት እንደሚገባ አስገንዝቧልም ተብሏል፡፡ በመስክ ምልከታው የታዩ ጠንካራ እና ደካማ ጎኖችን በመለየት የማጠቃለያ ሪፖርት ያቀረቡት የቋሚ ኮሚቴው አስተባባሪ የተከበሩ ወ/ሮ ታለፍ ፍታወቅ፣ በቀጣይ ትኩረት የሚሹ እና በፌዴራል ደረጃ ሊፈቱ የሚገቡ ጉዳዮችን በመተንተን የመፍትሔ አቅጣጫዎችን መስጠታቸውም ተዘግቧል። ለዋጋ ንረት እና ለኮንትሮባንድ ንግድ ምንጭ ስለሚሆን በክልሎች መካከል ፍትሐዊ የሆነ የነዳጅ አቅርቦት ሊኖር ይገባል ያሉት ደግሞ የክልሉ ምክትል አፈ-ጉባኤ የተከበሩ ወ/ሮ መነቴ ሙንዲኖ መሆናቸው ተዘግቧል።



የከተማ፣ መሠረተ ልማት እና ትራንስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አባላት፣ በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉብኝታቸው ወቅት፤

የኢፌድሪ እንደራሴዎች፣ በንግድ እና ቱሪዝም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴያቸው በኩል ወደ **ኦሮሚያ** ክልልም ለመስክ ጉብኝት ደርሰው ነበር። ቋሚ ኮሚቴውም፣ በጅማ ሙዚየም ተገኝቶ ታሪካዊ የመገልገያ ዕቃዎችን፣ ባህላዊ አልባሳቶችን እንዲኹም የጅማ አባጅፋር ቤተ መንግስትን እና የጅማ ከተማ አፎርቶማ መስጊድ ይዞታቸውን ጠብቀው እየታደሱ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ተዘዋውሮ መመልከቱ ተሰምቷል።

ክልሉ ያለውን እምቅ ሃብት ከማስተዋወቅ እና የአገር ውስጥም ሆኑ የውጭ ቱሪስቶችን በመሳብ ረገድ ተወዳዳሪነታቸውን ለማስፋት የተሰሩ ሥራዎች መኖራቸውን ቋሚ ኮሚቴው በጉብኝቱ ወቅት አንስቷል ተብሏል። ቋሚ ኮሚቴው በቡኖ በደሌ ዞን በንግድ፣ በቱሪዝም እና በመዋዕለ-ንዋይ ዘርፍ ያሉ የሥራ እንቅስቃሴዎችን ተመልክቶ፣ አካባቢውን የማስተዋወቅ ሥራ ላይ በትኩረት ሊሠራ እንደሚገባ ቋሚ አስገንዝቧል ተብሏል። የመስክ ቡድኑ አስተባባሪ የተከበሩ ወ/ሮ ሙሉ ይርጋ፣ በዞኑ መዋዕለ ንዋያቸውን ያፈሰሱ ባለ ሀብቶች የቴክኖሎጂ እና የዕውቀት ሽግግር እንዲኹም የሥራ ዕድል ፈጠራ ላይ ማኅበራዊ ኃላፊነታቸውን መወጣታቸውን እና የውጭ ምንዛሪ ማስገኘት መቻላቸውን በጥንካሬ አንስተው ውጤቱ ቀጣይነት እንዲኖረው ማበረታታት ያስፈልጋል ብለዋልም ተብሏል።


በንግድ እና ቱሪዝም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አባላት፣
በኦሮሚያ ጉብኝታቸው ወቅት፤

በወርኃ ታኅሣሥ በእንደራሴዎቹ ከተጎበኙት የከተማ አሥተዳደሮች መካከል **ድሬዳዋ** ስትገኝበት፣ ወደዚያች የከተማ አሥተዳደር የተጓዙትም በምክር ቤቱ የዲሞክራሲ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አባላት ናቸው ተብሏል። የቋሚ ኮሚቴው አባል እና የመስክ ቡድኑ አስተባባሪ የተከበሩ ወ/ሮ ዛራ ቢፍቱ፣ ምልከታው ከሪፖርት ግምገማ በተጨማሪ የተሰሩትን ሥራዎች በእቅዱ መሰረት ስለመከናወናቸው በአካል በቦታው በመገኘት እና በመገምገም የዲሞክራሲ ተቋማቱ እያጋጠማቸው ያለውን ተግዳሮት በመለየት መፍትሔ ለመስጠት ያለመ ምልከታ መሆኑን ገልፀዋል ተብሏል፡፡

የድሬዳዋአሥተዳደርምክርቤትአፈጉባኤክቡርአብዲ ሙክታር በበኩላቸው፣ ቋሚ ኮሚቴው በመስክ ምልከታው የሚፈለገውን ዓላማ እንዲያሳካ አሥተዳደሩ አስፈላጊውን ድጋፍ እንደሚያደርግ መግለጻቸው ሲዘገብ፤ ቋሚ ኮሚቴው የመስክ ምልከታውን ሲያጠቃልል የማጠቃለያ ግብረ-መልስ እንደሚሰጥ የመስክ ቡድኑ መሪ የተከበሩ ወ/ሮ ዛራ ቢፍቱ መናገራቸውን ከምክር ቤቱ የተገኘው ዘገባ ጠቅሷቸዋል።



የዲሞክራሲ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አባላት፣ በድሬ ዳዋ
የመስክ ጉብኝታቸው ወቅት፤

በወርኃ ታኅሣሥ የመስክ ጉብኝት ዕጣ የደረሳት ሌላይኛዋ ክልል **ሐረር** ስትሆን፣ ወደ ሐረር የደረሱትም በምክር ቤቱ የዲሞክራሲ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አባላት ነበሩ ተብሏል። የቋሚ ኮሚቴው አባል እና የመስክ ምልከታ ቡድኑ አስተባባሪ የተከበሩ ወ/ሮ ዛራ ቢፍቱ፣ የክልሉ መንግሥት ተፈናቃዮችን በመቀበል እና እንክብካቤ በማድረግ ላለፉት 8 ዓመታት መልካም ድጋፍ ሲያደርግ እንደነበር ገልፀው፣ ክልሉ በኹለት የጋራ መኖሪያ ቤት ሕንፃዎች ላይ ከ100 በላይ ለሚሆኑ ተፈናቃይ ዜጎች እየደረገ ያለው ሥራ የሚበረታታ መሆኑን በጥንካሬ አንስተዋል ተብሏል፡፡ የረድኤት ድርጅቶች በአሁኑ ወቅት እንደ ምግብ፣ መብራት፣ የጤና አገልግሎት ያሉ ድጋፎችን በማቋረጣቸው ተፈናቃዮች ለችግር እየተጋለጡ በመሆኑ ኢትዮጵያውያን የበኩላቸውን ድጋፍ እንዲያደርጉ ሲሉም የተከበሩ ወ/ሮ ዛራ መልዕክት ማስተላለፋቸው ተዘግቧል።

መካከል ሳይጠቀስ የማይታለፈው **አማራ** ክልል ሲሆን፣ ወደክልሉ መቀመጫ የሄዱትም፣ በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የከተማ መሠረተ ልማት እና ትራንስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አባላት ሲሆኑ፤ እነርሱም፣ በባህርዳር ከተማ የኅብረተሰቡን የልማት ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የተሰሩ የልማት ስራዎችን ለመመልከት የሚያስችል የመግቢያ ውይይት ከክልሉ የመሠረተ ልማት ቢሮ የሥራ ኃላፊዎች ጋር ውይይት አድርገዋል ተብሏል።

እኒኹ የኮሚቴው አባላትም፣ ከፍተኛ ሀብት ተመድቦላቸው የሚሰሩ የከተማዋ ፕሮጀክቶች የጥራት ደረጃቸውን ጠብቀው በተያዘላቸው ጊዜ፣ ወጪ እና ከሌብነት እና ከብክነት በፀዳ ሁኔታ መከናወናቸውን እንዲኹም የፕሮጀክቶቹ ክንውን የሚገኝበትን ደረጃ ማየት እና መለየታቸውን የመሳሰሉ ጉዳዮችን በመስክ ምልከታው እንደሚያረጋግጡ ተጠቅሷል።



የሐረሩ የመስክ ጉብኝት፤

በዚኽ የእንደራሴ ዕትም ሽፋን በሰጠነው ታኅሣሥ ወር ወደ ሌላይኛዋ ድንበርተኛ **አፋር** ክልል የተጓዙት በምክር ቤቱ የግብርና ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አባላት፣ ከክልሉ የእርሻ እና የተፈጥሮ ሀብት እና ከእንስሳት እና ዓሣ ሀብት ልማት ቢሮ የሥራ ኃላፊዎች ጋር የመግቢያ ውይይት አድርገዋል ተብሏል። የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ ሰለሞን ላሌ በውይይት መድረኩ ላይ ባስተላለፉት መልዕክት፣ በ2018 በጀት ዓመት ባለፉት ስድስት ወራት የተሰሩ ሥራዎች በመገምገም ጠንካራ ጎኖች ተጠናክረው እንዲቀጥሉ እና ውስንነት የሚታየባቸው ጉዳዮች እንዲሻሻሉ መሥራት እንደሚገባ ጠቁመዋል ተብሏል።

በግብርናው ዘርፍ የሚሰሩ ሥራዎች ምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ፣ ለዜጎች የሥራ ዕድል ለመፍጠር እንዲኹም የአገር ውስጥ ገቢ እና የውጭ ምንዛሬ ማሳደግ የዘርፉ ዋና ትኩረት እንደሆነም ሰብሳቢው ጨምረው ማስታወቃቸውን የምክር ቤቱ መረጃ ይጠቁማል። ቋሚ ኮሚቴው በውሎው የማዳበሪያ መጋዘን፣ በመስኖ እየለሙ ያሉ የበጋ ስንዴዎችን፣ የሱፍ እና የእንስሳት መኖ ማሳዎችን መጎብኘቱም ተዘግቧል።



የከተማ መሠረተ ልማት እና ትራንስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አባላት፣ በአማራ ክልል መቀመጫ ባሕር ዳር ከተማ ጉብኝታቸው ወቅት፤



የግብርና ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አባላት፣ በአፋር ጉብኝታቸው ወቅት፤

ክልሎች

# የፓርላማ ዲፕሎማሲ

በዚኽ ዕትም ሽፋን በሰጠነው ወርኃ ታኅሣሥ፣ የኢትዮጵያ እንደራሴዎች ሦሥት ፓርላመንታዊ ዲፕሎማሲን አከናውነዋል።

ቀዳሚው የእንደራሴዎቹ ፓርላመንታዊ ዲፕሎማሲ፣ አዲስ አበባ ውስጥ በተካሄደው፣ 7ኛው **የምሥራቅ አፍሪካ አገራት ፓርላማ ትብብር ጉባኤ** ላይ ነበር። በዚኹ፣ የሥነ-ምግብ እና የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ በተካሄደው ጉባኤ ላይ የተናገሩት የምክር ቤቱ አፈ-ጉባኤ የተከበሩ ታገሰ ጫፎ፣ ኢትዮጵያ በሌማት ትሩፋት እና በበጋ ስንዴ የምግብ ዋስትና እና ሥርዓተምግብ ላይ ተጨባጭ ውጤት አስመዝግባለች ብለዋል።

ኢትዮጵያ ይህን ዕውን ልታደርግ የቻለችው መንግስት እያካሄደ ባለው የኢኮኖሚ ማሻሻያ መሆኑን የጠቀሱት አፈ-ጉባኤው፣ ኢትዮጵያ የሥነ-ምግብ እና የምግብ ዋስትናን በማረጋገጥ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዜጎቿን ከድህነት ማውጣት መቻሏንም መናገራቸውን ከምክር ቤቱ የተገኘው መረጃ ጠቅሷቸዋል። የሥነ-ምግብን እና የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ የኢትዮጵያ እንደራሴዎች ምክር ቤትም፣ በቁጥጥር እና ክትትል እንዲኹም የፓርላማ ዲፕሎማሲ ሥራዎቹን አጠናክሮ እንደሚቀጥልም አፈ-ጉባኤው ጠቅሰዋል።

በምክር ቤቱ የመንግስት ረዳት ተጠሪ ሚኒስትር ዴኤታዋ የተከበሩ ወይዘሮ መሠረት ኃይሌ በበኩላቸው፣ መንግስት የምግብ ዋስትናን እና ሥነ-ምግብን ለማረጋገጥ ለግብርና መሣሪያዎች እና ሜካናይዜሽን ልዩ ትኩረት በመስጠት ዘርፈ-ብዙ የሌማት ትሩፋት ሥራዎችን እያከናወነ እንደሚገኝ ማብራራታቸውን ዘገባዎቹ ጠቅሰዋቸዋል። የምሥራቅ አፍሪካ አገራት የሥነ-ምግብ እና የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ የጀመሩትን የልምድ ልውውጥ አጠናክረው እንደሚቀጥሉ የተናገሩት ደግሞ፣ የምሥራቅ አፍሪካ አገራት ፓርላማ ትብብር ሊቀመንበሩ የተከበሩ አደን ሐጅ የሱፍ መሆናቸውን ከምክር ቤቱ የወጣው መረጃ ይጠቁማል።




ጉባኤው በከፊል፤

በወሩ የተካሄደው ኹለተኛው ፓርላመንታዊ ዲፕሎማሲ፣ በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የውጭ ግንኙነት እና የሠላም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፣ **ከጃፓን ልዑክ ጋር** ያደረጉት ውይይት ነበር። በውይይቱ የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ ዶ.ር. ዲማ ነጎ፣ ኹለቱ አገራት ረጅም ዓመታት በዲፕሎማሲ፣ በማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ግንኙነቶች ረጅም ታሪክ ያስቆጠሩ አገራት መሆናቸውን አስታውሰው፣ በንግድ፣ በሥልጣኔ እንዲኹም በቴክኖሎጂ ግንኙነታቸው ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጎለበተ መምጣቱንም ተናግረዋል ተብሏል።

ኢትዮጵያ የውጭ መዋዕለ ንዋይን በመሳብ በርካታ ሥራዎችን ማከናወኗን ጨምረው የገለጹት የተከበሩ ዶ.ር. ዲማ፣ ጃፓን በኢትዮጵያ የመዋዕለ-ንዋይ ዘርፍ እየተሳተፈች ያለችበትን መንገድ ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባልም ብለዋል ተብሏል። የጃፓን ልዑክ ቡድን መሪው የተከበሩ ኢንዶ ቶሺያኪ በበኩላቸው፣ ይኽ ዓይነቱ መድረክ የቆየውን የኢትዮጵያን እና የጃፓንን ወዳጅነት በተለያዩ ዘርፎች ለማጠናከር እና ወደ ተሻለ ደረጃ ለማሳደግ ጠቃሚ መሆኑን ገልፀዋል። ኢትዮጵያ ከአፍሪካ ኹለተኛውን የሕዝብ ቁጥር የያዘች እና በዕድገት ጎዳና ውስጥ ያለች አገር እንደመሆኗ፣ የባሕር በር ለማግኘት የምታደርገውን ጥረት እና የዓለም የንግድ ማኅበር አባል ለመሆን ለምታደርገው ጉዞ ድጋፏ ይቀጥላል ብለዋልም ተብሏል።



የውጭ ግንኙነት እና የሠላም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፣ ከጃፓኑ ልዑክ ጋር፤

የምስራቅ አፍሪካ ቀጠናን ሰላም እና ደህንነት ለማረጋገጥ ኹለቱ ምክር ቤቶች በትብብር እንደሚሠሩ፣ አፈ ጉባኤው የተከበሩ ታገሰ ጫፎ የተናገሩበት ደግሞ ሦሥተኛው የእንደራሴዎቹ ፓርላመንታዊ ዲፕሎማሲ ነበር። አፈ ጉባኤው ይህን የተናገሩት **በጅቡቲ ሪፐብሊክ ብሔራዊ ምክር ቤት ኘሬዚዳንት በተከበሩ ዲልታ መሐመድ ዲልታ ከተመራው የልዑካን ቡድን ጋር** በተወያዩበት ወቅት ነው ተብሏል፡፡

የተከበሩ ታገሰ፣ ኹለቱ አገራት የሚከተሉት የወደብ አጠቃቀም ሥርዓት በገቢ እና ወጪ ምርቶች የንግዱ አገልግሎት የተሣለጠ እንዲሆን አገዛው የጎላ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ ኢትዮጵያ ከጎረቤት አገሮች ጋር ያላት ግንኙነት መልካም መሆኑን ያነሱት አፈ-ጉባኤው፣ ኢትዮጵያ እና ጅቡቲ በኢጋድ ያላቸውን ተሳትፎ አጠናክረው እንዲቀጥሉ የኹለቱ አገራት ምክር ቤቶች በትኩረት መሥራት አለባቸው ብለዋልም ተብሏል። የጅቡቲ ሪፐብሊክ ብሔራዊ ምክር ቤት ኘሬዚዳንት ዲልታ መሐመድ ዲልታ በበኩላቸው፣ ኹለቱ አገራት የረጅም ጊዜ ታሪካዊ ግንኙነት እንዳላቸው ጠቅሰው፣ በምሥራቅ አፍሪካ ያለውን ሰላም በዘላቂነት ለማስቀጠል የጅቡቲ ሪፐብሊክ ብሔራዊ ምክር ቤት ከኢፌዴሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጋር በትብብር የሚሠራ መሆኑን ተናግረዋል፡፡



አፈ-ጉባኤው የተከበሩ ታገሰ ጫፎ፣ የጅቡቲ ልዑክን ባነጋገሩበት ወቅት፤

# የእንደራሴዎቹ ጉብኝት

የ ኢፌዴሪ እንደራሴዎች ምክር ቤት ምክትል አፈ-ጉባኤ የተከበሩ ወ/ሮ ሎሚ በዶን ጨምሮ፣ የምክር ቤቱ ከፍተኛ አመራሮች፣ አባላት እና የጽሕፈት ቤቱ ከፍተኛ አመራሮች በአምቦ ከተማ ያደረጉት ጉብኝትም አንዱ የምክር ቤቱ ክንውን ነበር። ወደ ከተማዋ ሲደርሱም፣ በከተማው ከፍተኛ አመራሮች፣ በአገር ሽማግሌዎች፣ በሀደ ሲንቄዎች፣ በወጣቶች እንዲኹም በከተማው ነዋሪዎች ከፍተኛ አቀባበል ተደርጎላቸዋል ተብሏል።

ምክትል አፈ-ጉባኤዋ ሎሚ በዶ የጉዞው ዓላማ የምክር ቤቱ ከፍተኛ አመራሮች በቱሪዝም ዘርፉ ከተሰሩት ሥራዎች መካከል አንዱ ወደሆነው ወንጪ ደንዲ ኢኮ ቱሪዝም መዳረሻ በአካል ተገኝተው ለማየት ነው ብለዋል። እንደራሴዎቹም በቆይታቸው፣ በኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ.ር. ዐቢይ አሕመድ ሀሳብ አመንጪነት በገበታ ለአገር ፕሮጀክት ከተገነቡ የቱሪዝም መዳረሻዎች አንዱ የሆነውን **የወንጪ-ደንዲ ኢኮ ቱሪዝም መንደር እና ሎጅን** ጎብኝተዋል ተብሏል።

ምክትል አፈ-ጉባኤዋ በዚኹ ወቅት እንደገለፁትም፣ በኹሉም አካባቢ የነበሩት ታሪካዊ ቦታዎች እና የተፈጥሮ ፀጋዎች ዛሬ የተፈጠሩ አይደሉም ማለታቸው ተዘግቧል። እነዚህን ፀጋዎች አልምቶ ለመጠቀም የተለየ እይታ እና አመራር የሚፈልግ በመሆኑ ለበርካታ ዓመታት አብረውን ቢኖሩም ሳንጠቀምበት ቆይተናል ያሉት የተከበሩ ሎሚ፣ አሁን ግን በጠቅላይ ሚኒስትር ዶ.ር. ዐቢይ አሕመድ ሀሳብ አመንጪነት እና አመራር ሰጪነት፣ ታሪካዊ ቦታዎቻችን እና የተፈጥሮ ፀጋዎቻችን ወደ ሀብትነት ተቀይረዋል ብለዋል ተብሏል።

በዚኽም ኢትዮጵያ ያላትን የተፈጥሮ፣ የታሪክ፣ የባህል እና ቅርስ እንዴት ከአባራ ወደ አሻራ መቀየር እና ጥቅም ላይ ማዋል እንደሚቻል ያሳዩ ፕሮጀክቶች መሆናቸውንም ምክትል አፈ-ጉባኤዋ ማብራራታቸውን ከምክር ቤቱ የተገኘው መረጃ ይጠቁማል። ወ/ሮ ሎሚ በዶ አክለውም፣ እንደቁርቆስ ገዳም ከ800 ዓመታት በላይ ተዘግቶ የቆየውን ገዳም፣ ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትራችን በአካል መጥተው በማየት ከእንግዳ መቀበል እስከ ታቦት ማደሪያ ድረስ እንዲሠራ እና በመንግስት ድጋፍ ያገኘ በመሆኑ አንድ ዓመት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ገዳሙ ለአካባቢው እና ለመላው የክርስትና እምነት ተከታዮች እንዲኹም ለጎብኚዎች ክፍት እንደሚሆን ገልፀዋል ተብሏል።



ምክትል አፈ-ጉባኤ የተከበሩ ወ/ሮ ሎሚ በዶ የተመራው የፓርላማ ቡድን፣ በአምቦ ጉብኝታቸው ወቅት፤

# እንደራሴዎቹ ስለ‘ራሳቸው በ‘ራሳቸው



የኢፌድሪ እንደራሴዎች፣ ታኅሣሥ ወርን ያገባደዱት ሕግጋት በማውጣት አልያም የሥራ አሥፈፃሚ ተቋማትን በመቆጣጠር ብቻም ሳይሆን፣ የሴት እንደራሴዎቹን ኮከስ ምክር ቤት የ2018 በጀት ዓመት የአምስት ወራት ዕቅድ አፈጻጸም በመገምገም እና ለእንደራሴዎቹ ሥልጠና በመስጠትም ነበር።

በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የሴቶች ኮከስ ሥራ አሥፈጻሚ፣ **የ2018 በጀት ዓመትን የአምስት ወራት የሥራ አፈጻጸም** መገምገሙ ቀዳሚው የወሩ ክንውን ነበር። የምክር ቤቱ ምክትል አፈ ጉባኤ እና የምክር ቤቱ ተመራጭ የሴቶች ኮከስ የበላይ ጠባቂዋ የተከበሩ ወ/ሮ ሎሚ በዶ፣ በኹሉም አካባቢ ያሉ ሴቶችን ተሳታፊ፣ ተጠቃሚ እና የውሳኔ ሰጭነት ሚናቸውን እንዲወጡ የአመራር ብቃትን ማሳደግ እንደሚገባ አስገንዝበዋል ተብሏል፡፡

ለ7[ተኛው] ዙር አገራዊ ምርጫ የሴቶችን ተሳትፎ ለማሳደግ የሚቻልበትን አሠራር ሥርዓት ለመዘርጋት ኮከሱ በኹሉም አካባቢዎች የግንዛቤ ሥረዎችን መሥራት እንደሚጠበቅበትም የተከበሩ ሎሚ በዶ መናገራቸው ተጠቅሷል። ምክትል አፈ ጉባኤዋ አያይዘውም፣ በአገራዊ ምክክር ኮሚሽን የሴቶች ተሳትፎ እንዲኖር እና የአመራር ተሳትፎን ለማሳደግ በኹሉም አካባቢዎች ትኩረት ተሰጥቶ መሠራት እንደሚገባ ጠቁመዋል፡፡ በምክር ቤቱ የጤና፣ ማኅበራዊ ልማት፣ ባህል እና ስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢዋ የተከበሩ ወ/ሮ ወርቅሰሙ ማሞ በበኩላቸው፣ ለዩኒቨርስቲ ሴት ተማሪዎች የተሰጠው ሥልጠና ለአገር ተረካቢ ዜጎች መሰረት የሚጥል በመሆኑ በቀጣይም ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት አመላክተዋል ተብሏል፡፡

የበጀት ዓመቱ  የአምስት ወራት የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርትን ለሥራ አስፈፃሚው በዝርዝር ያቀረቡት፣ የምክር ቤቱ ተመራጭ ሴቶች ኮከስ ምክትል ሰብሳቢዋ የተከበሩ ወ/ሮ አለሚቱ አበበ፣ የምክር ቤቱ የሴቶች ኮከስ ተልዕኮውን ከመወጣት አንፃር በበጀት ዓመቱ በርካታ ተግባራትን ማከናወን መቻሉን ጠቁመው፣ በቀጣይም ልምድ እና ተሞክሮዎችን በማስፋት ሴቶች በኹሉም አካባቢዎች አገራዊ ኃላፊነትን ለመወጣት በሚያስችል መልኩ በትኩረት እንደሚሠራ መናገራቸው ተጠቅሷል።



የሴት እንደራሴዎቹ ኮከስ ምክር ቤት የ2018 በጀት ዓመት የአምስት ወራት ዕቅድ አፈጻጸም ግምገማ፤

በወርኃ ታኅሣሥ፣ በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት ውስጥ ለሚገኙ ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢዎች፣ አባላት እና የሕግ ባለሙያዎች፣ **በሕግ ጉዳዮች ዓለም አቀፍ ትብብር ዙሪያ** የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥልጠና ተሰጥቷል።በሥልጠናው ላይ የፍትሕ ሚኒስትሯ ሐና አርዓያ ሥላሴ የተገኙ ሲሆን፣ ሥልጠናውም በሕግ ጉዳዮች ዓለም አቀፍ ትብብር፣ ከአገራት ጋር ያሉ ስምምነቶች፣ አሳልፎ ስለመስጠት፣ በወንጀል ጉዳዮች የጋራ የሕግ ትብብር፣ ፍርደኞችን ማስተላለፍ የሚሉት ዋና ዋና ነጥቦች ነበሩ ተብሏል።

በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የሕግ እና ፍትሕ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ የተከበሩ ወ/ሮ እፀገነት መንግሥቱ፣ ወንጀልን ለመከላከል በሚያግዙ እና በሕግ ጉዳዮች ዓለም አቀፍ ትብብሮች ዙሪያ የተሰጠው ሥልጠና ቋሚ ኮሚቴው በመመርመር ላይ ላለው የስምምነት ማፀደቂያ ረቂቅ ዐዋጆች ዙሪያ ግልፅነትን የሚፈጥር እና አጋዥ መሆኑን ገልፀዋል ተብሏል። ሰብሳቢዋ አክለውም፣ ቋሚ ኮሚቴው በቀጣይ ከቻይና፣ ብራዚል እና ከደቡብ አፍሪካ ጋር እንዲካሄዱ የቀረቡ ስምምነቶች ዓለም አቀፍ ደረጃቸውን ያሟሉ እንዲሆኑ፣ በየአገሩ የሚገኙ ዜጎች ፍርዳቸውን በአገራቸው እንዲፈፅሙ፣ አገራት ባላቸው ትብብር በወንጀል ድርጊት የተሳተፉ ዜጎችን አሳልፈው እንዲሰጡ ለማድረግ ጭምር እንደሚያስችሉም አስረድተዋል።



ሠልጣኞቹ እንደራሴዎች በከፊል፤

በወሩ ለእንደራሴዎቹ የተሰጠው ሌላይኛው ሥልጠና፣ **በአካል ጉዳተኞች አካታችነት ዙሪያ** የተካሄደ እንደነበር ከምክር ቤቱ የተገኘው መረጃ ይጠቁማል። ሥልጠናውን አስመልክቶ በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የጤና፣ ማኅበራዊ ልማት፣ ባህል እና ስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ የተከበሩ ወርቅሰሙ ማሞ፣ ኢትዮጵያ አካል ጉዳተኞች በተለያዩ የሕይወት ዘርፎች ኹሉ ወደኋላ እንዳይቀሩ እና በድህነት ውስጥ እንዲቆዩ የሚ ያደርጉ እንቅፋቶችን ለመፍታት ጥረት እያደረገች ትገኛለች ብለዋል። በሥልጠናው ላይም፣ በምክር ቤቱ የመንግስት ረዳት ተጠሪ ሚኒስትር ዴኤታዋን የተከበሩ ወ/ሮ ወይዘሮ መሠረት ኃይሌን ጨምሮ፣ የቋሚ ኮሚቴዎቹ ሰብሳቢዎች እና ምክትል ሰብሳቢዎች እንዲኹም የምክር ቤቱ ጽሕፈት ቤት ከፍተኛ አመራሮች መሳተፋቸው ተጠቅሷል።



በአካል ጉዳተኞች አካታችነት ዙሪያ የተካሄደው ሥልጠና በከፊል፤

ሦሥተኛው የእንደራሴዎቹ የወሩ ሥልጠና የአትኩሮት ማዕከል የነበረው፣ እንደራሴዎቹ የአሥፈፃሚ ተቋማትን የእቅድ አፈጻጸም ሪፖርትን ሲገመግሙ **የሰላምን አካቶ ትግባራ** የእቅዳቸው አካል አድርገው እንዲሰሩ ለማስቻል በሚል የተሰጠ እንደነበር ከምክር ቤቱ የተገኘው መረጃ ይጠቁማል። በርዕሰ-ጉዳዩ ላይ የተናገሩት ምክትል አፈ-ጉባኤዋ የተከበሩ ወ/ሮ ሎሚ በዶ፣ ሰላም ኹለንተናዊ በመሆኑ ከሰው ልጅ የአስተሳሰብ፣ የአመለካከት፣ ባህል እና እሴቶች፣ ከተፈጥሮ ሀብት ልማት እና ጥበቃ ጋር፣ ከመንግስት ፖለቲካዊ ሥርዓት እንዲኹም ለተረጋጋ መዋቅራዊ ሥርዓት እና አሠራሮች ትልቅ እንደምታ ያለው መሆኑን አስገንዝበዋል ተብሏል።

አፈ-ጉባኤዋ አክልውም፣ የዜጎች ነፃነት፣ እኩልነት እና አንድነት፣ ተሳታፊነት እና አካታችነት ሲጠናከር፣ በነፃነት የመንቀሳቀስ መብቶች ሲከበሩ፣ አገልግሎት እና ማኅበራዊ ጠቃሚነት ሲረጋገጥ ዘላቂ ሰላምን ማምጣት እንደሚቻል ተናግረዋል። ሰላምን በፍላጎት ብቻ የምናመጣው ጉዳይ አይደለም ያሉት የተከበሩ ወ/ሮ ሎሚ፣ ሰላማችንን አልፎም የማኅበረሰባችንን ሰላም ለማረጋገጥ እና ታላቋን ኢትዮጵያ ለመገንባት ኹላችንም የሚጠበቅብንን ኃላፊነቶች ሁሉ መወጣት ይኖርብናል ሲሉ ማሳሰባቸውን ከምክር ቤቱ የተገኘው መረጃ ጠቅሷቸዋል። በመድረኩም የምክር ቤቱ ከፍተኛ አመራሮች፣ የየቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢዎች እና ምክትል ሰብሳቢዎች፣ የሰላም ሚኒስቴር ሚኒስትር፣ ሚኒስትር ዴኤታዎች እና ከፍተኛ አመራሮች፣ የየክልል ምክር ቤቶች አፈ-ጉባኤዎች እና ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች ተገኝተው ነበር ተብሏል።



ሥልጠናው በከፊል፤



ጠቅላይ ሚኒስትር ናሬንድራ ሞዲ፣ ለኹለቱ ምክር ቤቶች ንግግር ባደረጉበት ወቅት ከጠቅላይ ሚኒስትር ዶ.ር. ዐቢይ አሕመድ፣ ከፌደሬሽን ምክር ቤት አፈ ጉባኤ የተከበሩ አገኘሁ ተሻገር እና ከሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ ጉባኤ የተከበሩ ታገሰ ጫፎ ጋር

# የሕንዱ ሰው ውሎ

ሥራውን ሊያጠናቅቅ ጥቂት ወራት የቀሩት ስድስተኛው የኢትዮጵያ እንደራሴዎች ምክር ቤት፣ ባሳለፋቸው ዐራት ዓመታት ካስተናገዳቸው መድረኮች ለየት ያለ አንድ መድረክም በዚኹ ታኅሣሥ ወርም አካሂዶ ነበር። መድረኩ፣ ‘የዲሞክራሲ ተጠቃሽ አገር’ የሚል ቅጽል የተሰጣት የሕንዱ ጠቅላይ ሚኒስትር የተገኙበት ነበር። በዕለተ ታኅሣሥ 28 ወደ እንደራሴዎቹ ምክር ቤት ብቅ ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትር ናሬንድራ ሞዲ፣ ለኹለቱም የፌዴሬሽን ምክር ቤቶች ግማሽ ሰዓት የፈጀ ሰፊ ንግግር አድርገዋል።

ሞዲ፣ ለፌዴሬሽን እና ለኣንደራሴዎቹ ምክር ቤት አባላት ባደረጉት ንግግርም፣ ኹለቱ አገራት ያላቸውን ታሪካዊ ግንኙነት በማንሳት አድንቀዋል። “በመካከላችሁ ስገኝ ታላቅ ደስታ ይሰማኛል፤ እዚህ በኢትዮጵያ የአንበሶች ምድር በመገኘቴ ትልቅ ኩራት ይሰማኛል” ያሉት ሞዲ፣ “ዛሬ በዓለም ደቡባዊ ክፍል ያለው ሕዝብ፣ እንደ ጥንታዊ ሥልጣኔ ባለቤት፣ እንደ ወዳጅ ኢትዮጵያ እና ሕንድ በጋራ ይቆማሉ” ሲሉም በኹለቱ አገራት መካከል ያለውን ትብብር ጠቅሰዋል። “በ1.4 ቢሊዮን ሕንዳውያን ስምም የወዳጅነት፣ የመልካም ምኞት እና የወንድማማችነት ሰላምታዬን አቀርብላችኋለሁ” ሲሉ የተደመጡት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ “በኢትዮጵያ ድር ቢያብር አንበሳ ያስር የሚል አባባል እንዳለ ተነግሮኛል። በሕንድ ደግሞ ልቦች የሚያብሩ ከሆነ ተራራ መግፋት ይችላሉ የሚል አባባል አለን፤ እውነትም አብሮነት ጥንካሬ ነው፤ ትብብር ኃይል ነው” ብለዋል።

የሕንዱ ሰው፣ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ.ር. ዐቢይ አሕመድ በተገኙበት ባደረጉት በዚህ ንግግር፣ በሕንድ እና በኢትዮጵያ መካከል ያለው ዘላቂ ትስስርን ጠንካራነትም አትተዋል። ጠቅላይ ሚኒስትሩም በንግግራቸው፣ በኹለቱ የጥንታዊ ሥልጣኔ ባለቤት አገራት መካከል ያለው ግንኙነት ወደ ስትራቴጂክ አጋርነት እና አዲስ ምዕራፍ የተሸጋገረበት ወቅት ላይ እንገኛለን ብለዋል። ባለፉት ዓመታት ኹለቱ አገራት በኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊ እና ዲፕሎማሲያዊ ዘርፎች ያላቸው ግንኙነት ማደጉን የጠቀሱት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ ሕንዳውያን ባለሀብቶች በጤና፣ በግብርና እና አምራች ዘርፎች ከ 5 ቢሊየን ዶላር በላይ መዋዕለ-ንዋይ በማፍሰስ ላይ እንደሚገኙም ተናግረዋል። ኹለቱ አገራት በያሉበት አህጉር ተፅዕኖ ፈጣሪ መሆናቸውንም ጠቅሰው፣ ለጋራ ተጠቃሚነት እና ብልፅግና በስትራቴጂካዊ ትብብር በጋራ እንሠራለን ሲሉ ተሰምተዋል።



ጠቅላይ ሚኒስትር ናሬንድራ ሞዲ፣ ለኹለቱ ምክር ቤቶች ንግግር ባደረጉበት ወቅት

በኢትዮጵያ እና በሕንድ መካከል ያለው ኹለንተናዊ ትብብር ተጠናክሮ ይቀጥላል ሲሉ የተናገሩት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ አገራቸው የምታደርገውን ድጋፍ ለማጠናከርም ያላቸውን ዝግጁነት ገልጸዋል።በቴክኖሎጂ ሽግግር፣ በሳይበር ደኅንነት፣ በአቅም ግንባታ፣ በግብርና፣ በትምህርት እና በጤና ላይ በትብብር ለመሥራት ዝግጁ መሆናቸውንም ተናግረዋል። ኹለቱ አገራት ስለሚጋሯቸው ታሪኮች፣ ቅርሶች እና ፍላጎቶች ያነሱት ጠቅላይ ሚኒስትር ናሬንድራ ሞዲ፣ በሕንድ እና በኢትዮጵያ ሕዝብ መዝሙር ውስጥ "አገር በእናት መመሰሏን" በማንሳት ያለውን ተመሳስሎሽ አስረድተዋል። ይህም የኩራት ምንጭ እና ለአገር ያለ ኃላፊነትን ያሳያል ሲሉም ሞዲ አክለዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ሞዲ፣ ከጠቅላይ ሚኒስትር ዶ.ር. ዐቢይ አሕመድ የአገሪቷን ከፍተኛ የክብር ኒሻንም ተሸልመዋል።

# ሹመት

የኤፌድሪ እንደራሴዎች፣ በወርኃ ታኅሣሥ የተወሰኑ ሹመቶችንም አጽድቀዋል። የሹመቶቹን የውሳኔ ሀሳቦች ያቀረቡት፣ በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የመንግስት ዋና ተጠሪ ሚኒስትሩ የተከበሩ ዶ.ር. ተስፋዬ በልጅጌ እንደነበሩ ተዘግቧል። ተሿሚዎቹም፣ ክብርት ወ/ሮ ሃይማኖት ዘለቀ ወርቅነህ የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙሃን ባለሥልጣን ዋና ዳይሬክተር እና 34 የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ዕጩ ዳኞች መሆናቸው ታውቋል። እንደራሴዎቹም፣ በዋና ተጠሪው የቀረበላቸውን የሹመቶቹን የውሳኔ ሀሳቦች፣ እንደቅደም ተከተሉ፣ የውሳኔ ሀሳብ ቁጥር 3/2018 እና የውሳኔ ሀሳብ ቁጥር 4/2018 ሲሉ በሙሉ ድምጽ እና በአንድ ድምጸ-ተዐቅቦ አጽድቀዋቸዋል።



ሠላሳ አራቱ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ዕጩ ዳኞች ቃለ-መሃላ ሲፈጽሙ፤



የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙሃን ባለሥልጣን ዋና ዳይሬክተር ሆነው የተሾሙት፣ ወ/ሮ ሃይማኖት ዘለቀ ወርቅነህ ቃለ-መሀላ ሲፈጽሙ፤

# የብሪጅ ዳሰሳዊ ምልከታ፦ ኢትዮጵያ፣ ሕንድ እና ሞዲ

የሕንዱ ጠቅላይ ሚኒስትር ናሬንድራ ሞዲ ባሳለፈነው ታኅሣሥ ሰባት፣ በኢትዮጵያ የመጀመሪያውን ይፋዊ ጉብኝት አድርገው ነበር። የአገራቸው የቀደሞው ጠቅላይ ሚኒስትር ማንሞሃን ሲንግ በኋላ ወደ ኢትዮጵያ በመምጣት ኹለተኛው የሕንድ ርዕሰ-መንግሥት የሆኑት ሞዲ፣ ከኢትዮጵያው ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ.ር. ዐቢይ አሕመድ እጅ የአገሪቷን ከፍተኛ የክብር ኒሻን ከመሸለማቸው ባለፈ፣ በኢትዮጵያ እንደራሴዎች ምክር ቤት ተገኝተውም፣ ግማሽ ሰዓት የፈጀ ሰፊ ንግግር አድርገዋል። አኹን ያለውን የኢትዮጵያ እንደራሴዎች ምክር ቤት ያቋቋመው ሕገ-መንግሥት ከጸደቀበት ጊዜ አንስቶ፣ በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት በመገኘት ንግግር በማድረግም ኹለተኛው የአገር መሪ ሆነዋል። እነሆ ይኽች የታኅሣሥ የእንደራሴ ዕትምም፣ ስለ ኢትዮ-ሕንድ ነባር ዝምድና፣ አኹነኛ ስምምነቶች እና ስለ ሕንዱ ሰው ጥቂት ነጥቦችን አስተሳስራ መዳሰስን መርጣለች።

## ምስር ምን ብላ ነበር?

መንበረ-ሥልጣን ላይ ሳሉ፣ በኢፌድሪ የእንደራሴዎች ምክር ቤት ተገኝቶ ንግግር በማደረግ፣ የመጀመሪያው መሪ ግብጹ ፕሬዝደንት አቡዱል ፈታህ አልሲሲ ናቸው። ፕሬዝዳንቱ፣ መጋቢት 14 ቀን 2007 ዓ.ም. ካርቱም ላይ የታላቁ ሕዳሴ ግድብ የመርህ ስምምነትን ከፈረሙ በኋላ፣ በቀጥታ ወደ አዲስ አበባ በመምጣት ነበር፣ መጋቢት 16 ቀን በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት ንግግር ለማድረግ የተሰየሙት። በዚያኑ ዕለትም ከቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለማርያም ደሳለኝ ጋር በቤተ-መንግሥት የሁለትዮሽ ውይይት አድርገው እንደነበር ይታወሳል። ፕሬዝዳንት አልሲሲ ለኢትዮጵያ እንደራሴዎች ባደረጉት ንግግርም፣ የአባይ ወንዝ ውኃን በጋራ ስለመጠቀም ስላላቸው ተስፋ እና ስጋት ጠቃቅሰው ነበር።

አልሲሲ፣ የኢትዮጵያን የመልማት ጥረቶች እንደሚረዱ ገልጸው፣ ነገር ግን ሀብቶችን ለመጠቀም እና እድገትን ለማምጣት በሚደረገው ጥረት ግጭቶች መወገድ እንዳለባቸው ወደ ማስጠንቀቅም ተሻግረው ነበር። የግብፅ ወንድሞቻችሁም የማልማት መብት ብቻ ሳይሆን፣ የመኖር መብትም እንዳላቸው እንዳትዝነጉ ሲሉም ተደምጠዋል። ወደ 15 ደቂቃ በፈጀው ንግግራቸው፣ ከመምጣታቸው በፊት የተፈራረሙት ስምምነት፣ ልዩነቶችን እና በናይል ተፋሰስ ኢኒሼቲቭ ማዕቀፍ ስምምነት ውስጥ ያሉ ያልተቋጩ ነጥቦችን እንድንሻገር የሚያስችለን፣ ኹሉንም የተፋሰስ አገራት የሚያካትት እና ኹሉንም ፍላጎቶቻቸውን የሚመልስ መሆን አለበትም ብለው ነበር። በቀጣናው ውስጥ የሚታዩ በርካታ ችግሮችን በማንሳትም፣ ‘ርሳቸው “የሽብርተኝነት ወረርሽኝ” በማለት የጠሩት ስጋት በከፍተኛ ኹኔታ እየተስፋፋ መሆኑን በማስጠንቀቅ፣ የ‘ሱን ተፅዕኖ ለመግታት በአገራት መካከል ተጨማሪ ትብብር እንደሚያስፈልግ ገልጸው፣ እንደራሴዎቹን ተሰናብተዋል።

## “ምስጋናዬን ተቀበሉኝ”

“የጥንታዊት ታሪክ እና የገናና ሥልጣኔ ባለቤት፣ የጥቁር ሕዝብ ታላቅ የነጻነት ተጋድሎ ትዕምርት ከሆነች አገር፣ ይሄ የክብር ኒሻን ስለተበረከተልኝ ደስታዬ ብዙ ነው፤ እነሆ 1.4 ቢሊዮን በሚሆነው የአገሬ ሕዝብ ስም ምስጋናዬን ተቀበሉኝ”

ይሄ ንግግር፣ ከታሪክ መጸሕፍት የተወሰደ አልያም ከቲያትር ገጾች የተቀዳ አይደለም። ታኅሣሥ 8 ማምሻ ላይ በኢትዮጵያ አደባባይ ላይ የተነገረ እንጂ፤ ተናጋሪውም፣ የታላቋ ዲሞክራሲ አገር የሚል ቅጽል የተሰጣት፣ የሕንዱ ጠቅላይ ሚኒስትር ናኤድራ ሞዲ ነበሩ። ሞዲ ይኽንን ሞቃታማ ቃላት የሞላበት ንግግር ያደረጉት፣ ከኢትዮጵያው ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ.ር. ዐቢይ አሕመድ እጅ፣ የኢትዮጵያን ከፍተኛ የክብር ኒሻን አንገታቸው ላይ ባጠለቅቁበት ኩነት ነበር።

በዚያ የክብር ጉባኤ ላይ ንግግር ያደረጉት ዶ.ር. ዐቢይ አሕመድም፣ የኢትዮጵያ እና ሕንድ ትብብር ለደቡብ ደቡብ አጋርነት ትልቅ አቅም ነው ሲሉ ተደምጠዋል። ጠቅላይ ሚኒስትሩ በዚኹ ምሽት ባደረጉት ንግግር፣ አሁን ላይ በኹለቱ አገራት መካከል የተፈጠረው ስትራቴጂክ ግኑኙነት እያደገ በሕዝቦች መካከል የባህል ትስስር ፈጥሯል ብለዋል፡፡ በኢትዮጵያ እና በሕንድ መካከል ለ1000 ዓመታት የዘለቀው ታሪካዊ ግኑኙነት በዲፕሎማሲ፣ በንግድ፣ በትምህርት እና በባህል ልቆ ወደ ስትራቴጂካዊ ትብብር መሻገሩንም ጠቅላይ ሚኒስትሩ አንስተዋል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ናሬንድራ ሞዲ በአፍሪካ አህጉር ላይ ያላቸውን ወጥ አቋም ያደነቁት ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ.ር. ዐቢይ አህመድ፣ ሌሎች ወዳጅ አገራትም በዚህ ላይ አጋርነታቸውን ማጠናከር አለባቸው ብለዋል። በጋራ ትብብር ላይ የተመሰረተው የኢትዮጵያ የእድገት አቅጣጫ ከአፍሪካ የመነጨ፣ በአፍሪካዊ እሳቤ የሚመራ እና በአፍሪካ የሚተረጎም ነውም ሲሉ ተናግረዋል፡፡ ኢትዮጵያ ሉዓላዊነትን ያከበረ ዘመኑን የዋጀ አጋርነት እና ተጨባጭ ትብብር ከሕንድ ጋር ማድረግ ትፈልጋለች ብለዋል፡፡ የኹለቱ አገራት ግንኙነት በእኩልነት ላይ የተመሰረተ መሆን እንዳለበት ያነሱት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ በደቡብ ዋልታ ጥምረት መርህ ላይ ያተኮረ መሆን እንዳለበትም ጠቅሰዋል፡፡

የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ጠንካራ እድገት እያሳያ መሆኑን የገለጹት ዶ.ር. ዐቢይ፣ ባለፈው ዓመት 9.2 በመቶ እድገት ማሳየቱን ገልጸው፣ በዘንድሮ በጀት ዓመት ደግሞ 10.3 በመቶ እድገት ያስመዘግባል ተብሎ ይጠበቃል ብለዋል፡፡ በኢትዮጵያ 650 የሕንድ ኩባንያዎች በተለያዩ የመዋዕለ-ንዋይ ዘርፎች ተሰማርተው እንደሚገኙ የጠቀሱት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ፣ ይህን ወደ ጠንካራ ትብብር ማሳደግ እንደሚቻል በመናገር፣ ለሕንዱ አቻቸው የተዘጋጀውን የእራት ግብዣ ደምድመዋል።

## የጉብኝቱ ፋይዳ

የሕንድ ጠቅላይ ሚኒስትር ናሬንድራ ሞዲ፣ በኢትዮጵያ ከታኅሣሥ 7 እስከ 8 ቀን 2018 ዓ.ም ድረስ የቆየ ታሪካዊ የተሰኘ ጉብኝት አድርገዋል። ጉብኝቱ ኢትዮጵያ በሕንድ የአፍሪካ ፖሊሲ ማዕቀፍ ውስጥ ያላትን እየጨመረ የመጣውን የኢኮኖሚ ትስስር፣ የኹለገብ ልማት እና ስትራቴጂካዊ ትብብር፣ እንዲሁም የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነትን ከማጉላቱ ባሻገር ኢትዮጵያ በአፍሪካ አህጉር ዋንኛ ዲፕሎማሲያዊ ማዕከል መሆኗን ያስረገጠ ነውም ተብሎለታል።

የሞዲ ጉብኝት፣ ከተለመደው የዲፕሎማሲያዊ ወዳጅነት ባለፈ ሕንድ ከአፍሪካ ጋር ያላትን ወዳጅነት ይበልጥ ለማጠናከር እና የዓለም ዓቀፉን የደቡብ ድምፅ በጋራ ለማጉላት ያላት ፍላጎት መጨመሩንም እንደሚያሳይ ብሪጅ ትገነዘባለች። እንደ ብሪጅ መረዳትም፣ የሞዲ የኹለት ቀናት ክራሞት በበርካታ ቁልፍ ጉዳዮች ላይ የኹለትዮሽ ትብብርን ለማጠናከር ያለመ ነው፤ ለማሳያ ያህልም፤

- የኢኮኖሚ እና የመዋዕለ-ንዋይ ትስስርን ማጠናከር፦ ሕንድ በኢትዮጵያ ከሚገኙ ዋና ዋና ቀጥተኛ የመዋዕለ-ንዋይ ፈሰስ አድራጊ አገር አንዷ ናት። ጉብኝቱ የንግድ ልውውጡን ለማሳደግ እና የሕንድ ኩባንያዎች በትምህርት፣ በጤና፣ በማኑፋክቸሪንግ እና በግብርናው ዘርፍ ያላቸውን ተሳትፎ ለማስፋት ያለመ መሆኑም ግልጽ ነው። ከዚኽ ባለፈም፣ ኢትዮጵያ ለጀመረችው የዐብይ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ሕንድ ያላትን የፋይናንስ እና ሙያዊ ድጋፍ ማረጋገጥ ዋነኛው የጉብኝቱ ፋይዳ ነበር

- የቴክኖሎጂ ሽግግር እና አቅም ግንባታ፦ ሕንድ በተለይ በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ እና በመድኃኒት ምርት ዘርፎች የላቀ ልምድ ያላት አገር መሆኗ ብዙ የተጻፈበት ነው። ጉብኝቱም፣ ኢትዮጵያ የዲጂታል ኢኮኖሚዋን እንድትገነባ እና የሰው ኃይሏን እንድታሰለጥን ሕንድ የምታደርገውን የልምድ ልውውጥ እና የቴክኖሎጂ ሽግግር ለማፋጠን ይረዳል ብላ ብሪጅ ታምናለች። ሕንድ በርካታ ኢትዮጵያውያን ተማሪዎችን በነጻ የትምህርት ዕድል ዛሬም ድረስ ሳታቋርጥ መቀበሏ፣ ኢትዮጵያ አብዝታ የምታሻውን የሠለጠነ ሰዋዊ ልማትን ይደግፋል።

- ዓለም ዓቀፍ እና ቀጠናዊ ጉዳዮች ላይ ያለ ተናባቢነት፦ ኢትዮጵያ እና ሕንድ በአፍሪካ ኅብረት እና በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ውስጥ በዓለም ዓቀፍ የፖለቲካ እና የደኅንነት ጉዳዮች ላይ በጋራ የመሥራት ሰፋ ያለ ልምድ አላቸው። የሞዲ ጉብኝትም፣ ኹለቱ አገራት የአፍሪካ ቀንድ ሰላም፣ የ.ተ.መ.ድ. የጸጥታው ምክር ቤት ማሻሻያ እና የብዝሓነት አስፈላጊነት ላይ ያላቸውን የጋራ አቋም የሚያጠናክሩበትን ዕድል መስጠቱን መጥቀስ ያሻል።

ከዚኽ ባለፈም፣ ኢትዮጵያ የአፍሪካ ኅብረት መቀመጫ እንደመሆኗ እና ከብሪክስ አባልነት በኋላም፣ ሉላዊው ደቡብ በተሰኘው እና ታዳጊ አገራትን ባሰባሰበው እና በዓለም ዓቀፍ ውሳኔዎች ላይ የራሱን ድምፅ ለማሰማት እየጣረ በሚገኘው ግዙፍ የፖለቲካ እና የኢኮኖሚ ስብስብ ውስጥ፣ በሚደረጉት እንቅስቃሴዎች ውስጥ መዳፏን ማሳረፍ መጀመሯ፣ የጠቅላዩን ጉብኝት ፋይዳ በዛ ያደርገዋል ብላ ብሪጅ ታምናለች።

## ዋናው ንግድ ነው!

ሕንድ ከኢትዮጵያ ጋር በንግድ፣ በቀጥታ የመዋዕለ-ንዋይ ፍሰት እና በባህል መስኮች ጭምር በትብብር እየሰራች ትገኛለች፡፡ አገራቱ፣ ከቅርብ አስርት አመታት ወዲህ ወደ ጠንካራ እና ዘርፈ ብዙ የንግድ እና የኢኮኖሚ አጋርነት ያደገ እና ታሪካዊ ጉልህ ግንኙነት አላቸው። ሕንድ ወደ ኢትዮጵያ ከምትልካቸው ምርቶች ውስጥ የመድኃኒት ምርቶች፣ ማሽነሪዎች፣ የብረት ውጤቶች፣ ተሸከርካሪዎች፣ የኤሌክትሪክ እቃዎች፣ ፕላስቲኮች እና የወረቀት ውጤቶች በቀዳሚነት ሲጠቀሱ፤ ኢትዮጵያ ደግሞ ወደ ሕንድ ከምትልካቸው ምርቶች መካከል ጥሬ ቆዳ እና ሌጦ፣ ጥራጥሬ፣ ቅመማ ቅመም እና ቡና ቀዳሚውን ድርሻ ይይዛሉ።

አገሪቷ በኢትዮጵያ ውስጥ ካሉ ከፍተኛ የውጭ ባለሀብቶች መካከልም አንዷ ነች። የቅርቦቹ ቁጥሮች እንደሚመሰክሩት፣ ከ650 በላይ የሕንድ ኩባንያዎች በኢትዮጵያ መዋዕለ ንዋያቸውን ያፈሰሱ ሲሆን፣ ፈቃድ የወሰዱትን ባለሀብቶችን እዚኹ ላይ ስናክላቸው ደግሞ፣ የመዋዕለ ንዋይ ፍሰቱ በርካታ ቢሊዮን ዶላርን ይሻገራል። በሥራ ላይ ያሉት እና በቀጣዮች ጊዜያት ወደ ሥራ ይገባሉ ተብለው የሚጠበቁት ባለሀብቶች የተሰማሩባቸውን ንዑስ የኢኮኖሚ ክፍሎች ስንመለከትም፣ የአገራቱ ትብብር ለኢትዮጵያ ዐብይ ኢኮኖሚ ያለውን ፋይዳ ይጠቁመናል። እነዚኽ ንዑስ የኢኮኖሚ ክፍሎችም ጨርቃ ጨርቅ እና አልባሳት፣ የቆዳ ማቀነባበሪያ፣ ስኳር፣ ግብርና ላይ የተመሰረቱ ኢንዱስትሪዎች፣ ፕላስቲኮች እና ሴራሚክስ፣ ግብርና እና የአበባ ልማት ዋናዎቹ ናቸው።

በርካታ የሕንድ ኩባንያዎችም ትልልቅ የንግድ እርሻዎችን የሚመሩ ሲሆን፣ በኢትዮጵያ ከፍተኛ ትርፍ በሚያስገኘው የአበባ ውጭ ምርት ኢንዱስትሪ ውስጥም ዋንኞቹ ተዋንያን ናቸው። የሕንድ ቴክኒካል እና ኢኮኖሚ ትብብር በተሰኘው መዋዕቅርም ኢትዮጵያ ከፍተኛዋ ተጠቃሚ አገር ነች። ከዚኹ በተጨማሪም፣ በርካታ ኢትዮጵያውያን በሕንድ በአሥተዳደር፣ በአይቲ፣ በሥራ ፈጠራ እና በዲፕሎማሲ መስኮች ጭምርም እየሠለጠኑ እንደሚገኙ ልብ ይሏል።

## ጥቂት ወደኋላ

ጥንታዊት እና የገናና ሥልጣኔ ባለቤት የተባለችው ኢትዮጵያ እና በመሰል ጥንታዊነት ስሟ የሚነሳው ሕንድ፣ ከኹለት ሺህ ዓመታት በፊት በሕንድ ውቅያኖስ እና በቀይ ባሕር አማካኝነት የአፍሪካን ድንበር የተሻገረ የንግድ ግንኙነት እንደነበራቸው፣ ድርሳናቱም ሆኑ የአርኪዮሎጂ ግኝቶች ይመሰክራሉ። በጥንታዊት ሕንድ የነበረው የኩሻን ሥርወ-መንግሥት ዘመን መገበያያ የነበሩ የወርቅ ሳንቲሞች፣ በአክሱም እና በደብረ ዳሞ ገዳማት መገኘታቸውም ተጽፏል። የሕንድ የጉፕታ ዘመነ-መንግሥት አሻራ የሆኑ የዘመኑ ቁሳቁሶች፣ የከበሩ ጌጣጌጦች እና ጨሌዎች በጥንታዊቷ አክሱም ወደብ በነበረችው አዶሊስ መገኘቱም ከተጻፈ ሦሥት ትውልድ ተሻግሯል። ሌሎች ዘመኑን መስካሪ የጉዞ ማስታወሻዎችም፣ የእነ ኢዛና የዝሆን ጥርስ፣ ወርቅ እና ዕንቁ፣ ቀይ ባሕርን ተሻግረው አክሱምን ከሕንድ ጋር እንዳገበያዮት ተርከዋል።

ኢትዮጵያ እና ሕንድ ግንኙነታቸው ዘመናትን እንዳስቆጠረ ምስክር ከሚሆኑ ተግባራት መካከል፣ ሕንድ ከእንግሊዝ ነጻነቷን ከተጎናጸፈች በኋላ ለሕንድ ዕውቅና በመስጥት ከቀዳሚዎቹ አገራት ተርታ የመሆኗ የታሪክ ሃቅ ነው። ኢትዮጵያ እና ሕንድ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነታቸውን የጀመሩት እ.አ.አ በ1948 ሲሆን፣ ከአፍሪካ አገራትም በሕንድ ኤምባሲዋን የከፈተችው የመጀመሪያዋ አገርም አድርጓታል። ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ፣ ኹለት ጊዜ (እ.አ.አ በ1956 እና በ1958) በሕንድ ያደረጓቸው ጉብኝቶች ለኹለቱ አገራት ግንኙነት መጠናከር መሠረት እንደጣሉ ይጠቀሳል፡፡

የሕንድ ሕዝብ እና መንግስት ከኢትዮጵያ ጋር ያላቸው ግንኘነት አንዱ ማሳያ በትምህርት ዘርፍ ያላቸው የኹለትዮሽ ግንኙነት እንደሆነ ይጠቀሳል፡፡ በርካታ ኢትዮጵያውያን በሕንድ ትምህርታቸውን የመከታተል ዕድል ሲያገኙ፣ የሕንድ ዜጎች ደግሞ በኢትዮጵያ በመምህርነት በማገልገል ቀዳሚዎቹ የባሕር ማዶ ሰዎች ናቸው። በአዲስ አበባ ከተማ የሚገኘው በኢትዮጵያ እና ሕንድ ማኅበረሰብ ድጋፍ የተቋቋመው ጋንዲ መታሰቢያ ሆስፒታልም፣ የአገራቱ ወዳጅነት ትዕምርት ሆኖ ተቀጥሯል። ምንም እንኳን ደርግ ቢያነሳውም ቅሉ፣ ሕንድ በአዲስ አበባ ከተማ ፒያሳ ላይ፣ ለአጼ ኃይለ ሥላሴ ሀውልት አቁማም ነበር።

በግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዘመነ መንግሥት የጀመረው የአገራቱ ጠበቅ ያለ ግንኙነት፣ መንግሥታት ቢቀያየሩም ተጠናክሮ ሰነብቷል። ኢትዮጵያ እና ሕንድ ከሁለት ሺህ ዓመታት የተሻገረ ሁለንተናዊ ግንኙነት እንደነበራቸው የተለያዩ መዛግብት ያስረዳሉ። ከ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮም በርካታ የሕንድ ተወላጆች ኢትዮጵያን የኑሮ ምርጫቸው እንዳደረጉ የሚያመለክቱ በርካታ ማሳያዎች አሉ።

በአንደኛውና በሁለተኛው የዓለም ጦርነት መካከል በነበሩት ዓመታት በርከት ያሉ ሕንዳውያን በተለያዩ የኢትዮጵያ ከተሞች በንግድ ሥራ ላይ ተሰማርተው ቆይተዋል፡፡

በፈረንጆቹ 1948 ኢትዮጵያ ከሕንድ ጋር መደበኛ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት የመሰረተች ሲሆን፣ በአምባሳደር ደረጃ ግንኙነታቸውን ያሳደጉትም በፈረንጆቹ ከ1952 ጀምሮ እንደሆነ መረጃዎች ያሳያሉ። በወቅቱ በርካታ ሕንዳውያን መምህራን ወደ ኢትዮጵያ በመምጣት በየጠቅላይ ግዛቱ ባሉ ትምህርት ቤቶች ውስጥ በማስተማር ላይ ቆይተዋል። ከኹለት ትውልድ በላይ የተሻገረው የአገራቱ የትምህርት ዘርፍ ትብብር፣ የኢትዮጵያን የከፍተኛ ትምህርት አቅም ለማሳደግ ያስቻለ ሲሆን፤ በርካታ ኢትዮጵያውያንም በሕንድ ኹለተኛ እና ሦሥተኛ ዲግሪ እንዲያገኙ በማድረግ የተማረ የሰው ኃይልን በማሟላት በኩል ሚናውን ተጫውቷል። የብሔሮች፣ የሃይማኖቶች፣ የባህሎች እና የመልክአ-ምድር ስብጥሮች ኢትዮጵያ እና ሕንድን እንደሚያመሳስላቸው እና ያሉበት ጂኦፖለቲካዊ ቀጠናም በፖለቲካ እና በውጭ ግንኙነት እንዲተባበሩ አስችሏቸዋል ይባልላቸዋል፡፡ የኢትዮጵያ እና የሕንድ የዲፕሎማሲ ግንኙነት አገራቱ በኢኮኖሚ፣ ፖለቲካ እና ማኅበራዊ መስክ እያስተሳሰረ ላለፉት 74 ዓመታት ዘልቋል።

## የቀደመው ስምምነት

ኢትዮጵያ እና ሕንድ፣ ጠንክራ ተብሎ ሊጠራ የሚችለውን ስምምነት የተፈራረሙት፣ ከጠቀስነው የጠቅላይ ሚኒስትር ሞዲ ጉብኘት ቀደም ብሎ ነበር። በኹለቱ አገራት መካከል ያለውን የቆየ የኹለትዮሽ የመከላከያ ግንኙነት ያጠናክራል የተባለለት የመጀመሪያው የጋራ የመከላከያ ትብብር ስብሰባን በሕንዷ ዋና ከተማ ኒው ዴሊህ አካሂደው ነበር። ስብሰባው በሕንድ የመከላከያ ሚኒስቴር ጸሐፊ አሚታብህ ፕራሳድ እና በኢትዮጵያ የመከላከያ የውጭ ግንኙነት እና ወታደራዊ ትብብር ዳይሬክተር ጄኔራል ሜጀር ጄኔራል ተሾመ ገመቹ በጋራ ለቀመንበርነት የተመራም ነበር። ኹለቱ አገራት የቀደመ የመከላከያ ትብብራቸውን ገምግመው ሥልጠና፣ የጋራ ወታደራዊ ልምምዶች፣ የህክምና ትብብር እና ከመከላከያ ኢንዱስትሪ ጋር የተያያዘ አዲስ ትብብር የሚሆኑ ዘርፎች ዙሪያ መወያየታቸውን የሕንድ ዜና ምንጮች ዘግበዋል።

የመከላከያ አጋርነቱን ለማጠናከር ያላቸውን የጋራ ቁርጠኝነት በማረጋገጥ፣ የመከላከያ ትብብር ተግባራትን አጠናክሮ ለማስቀጠል መስማማታቸውም ተጠቅሶ ነበር። ይህ የጋራ የመከላከያ ትብብር ስብሰባ፣ ቀደም ሲል በ2017 ዓ.ም. በኹለቱ አገራት የመከላከያ ሚኒስትሮች መካከል በተፈረመው የመግባቢያ ሰነድ መሠረት የተቋቋመ ተቋማዊ ማዕቀፍ አካል መሆኑም ተነግሯል። የመግባቢያ ሰነዱ፣ በመከላከያ ጉዳዮች ላይ መደበኛ የልውውጥ እና የስትራቴጂክ ውይይት ሥርዓት ያቀርባል። ኢትዮጵያ ከ1950ዎቹ ጀምሮ ሕንድ በአፍሪካ ካሏት ቁልፍ የመከላከያ አጋሮች አንዷ መሆኗም ይታወቃል። እያደገ የመጣው የመከላከያ ግንኙነት ከጥቅምት 4 እስከ ጥቅምት 6/2018 ዓ.ም በኒው ዴሊ በተካሄደው የተባበሩት መንግስታት የሰላም አስከባሪ ኃይል አስተዋጽኦ አድራጊ አገራት አዛዦች ጉባኤ ላይ የኢትዮጵያ ጦር አዛዥ መገኘታቸውም ተገልጿል።

ከዚያ ስምምነት ቀደም ብሎም፣ በመጋቢት 2017 ዓ.ም. ኹለቱ መንግስታት በሥልጠና እና በገንዘብ ድጋፍ የኢትዮጵያን ወታደራዊ አቅም ለማጠናከር ያለመ የመከላከያ ትብብር ስምምነትን በማጠናቀቅ ላይ እንደሆኑ አስታውቀው ነበር። በሕንድ የኢትዮጵያ አምባሳደር ደመቀ አጥናፉ በወቅቱ እንደተናገሩት፣ ስምምነቱ የረጅም ጊዜ የመከላከያ ትብብር ቀጣይነት ሲሆን፣ ሕንድ በ1950ዎቹ የሐረር ወታደራዊ አካዳሚን በማቋቋም እና በቀጣይ የሥልጠና ተነሳሽነቶች ያደረገችውን ድጋፍ አስታውሰዋል። ይህ ተነሳሽነት ሕንድ በአፍሪካ ዙሪያ የመከላከያ ትብብሯን በማስፋፋት የክልላዊ ደኅንነትን ለማሳደግ እና የኹለትዮሽ ግንኙነቶችን ለማጠናከር ከምትከተለው ሰፊ ጂዖፖለቲካዊ ስትራቴጂ ጋር የሚጣጣም መሆኑም ሲጠቀስ ተሰምቷል።

## ሰውየውን በጨረፍታ

የሕንዱ ጠቅላይ ሚኒስትር ናሬድራ ሞዲ፣ አንደበተ-ርትዑ መሪ ናቸው። ተናግሮ ማሳመን ጥርሳቸውን የነቀሉበት ዘዬ ነው። በዛ ላይ የሥነ-ጽሑፍ እና የትያትረኛነት ተሰጥኦቸው ሰዎችን የማሳመን እና የመቀስቀስ ልዩ ተሰጥዖን አጎናጽፏቸዋል። ሰውዬው የንግግር ብቻ ሳይሆኑ የማያወላዳ ውሳኔ በመስጠትም ስማቸው ይነሳል። የሕንድ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 370 ካሽሚር ለሚባለው ግዛት ራስን በራስ የማሥተዳደር መብት የሚፈቅድ ነበር። ሞዲ ይሄን ልዩ ሕገ-መንግሥታዊ ሥልጣን በመሰረዝ፣ አካባቢው ከቀሪው ሕንድ ጋር እንዲዋሓድ ያስተላለፉት ደፋር ውሳኔ፣ የሰውዬውን መስመር ተሻጋሪነት በቅጡ ያሳየ ነው ይባልለታል።

በእንግሊዝ ቅኝ ግዛት ዘመን የነበሩ አሮጌ ሕግጋትን ቀዳድደው በመጣልም፣ በአዲስ ሕንዳዊ ዕሴቶች ላይ በተመሰረቱ ሕግጋት ተክተዋቸዋል። በሕንድ የእንደራሴዎች ምክር ቤት እና በክልል ምክር ቤቶች 33 በመቶ መቀመጫ ለሴቶች እንዲጠበቅ የሚያዝ ሕግ ያፀደቁትም ‘ርሳቸው ናቸው። ከ34 ዓመታት በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ የትምህርት ፖሊሲውን በመቀየር፣ ተማሪዎች በተግባር እና በፈጠራ ላይ እንዲያተኩሩ አድርገዋል። ከአገሪቱ ሕዝብ ግማሹን እንደሚሸፍን የሚነገርለት የአገሪቱ ወጣት፣ ለሥራ ዝግጁ የሚያደርግ የሙያ ሥልጠና በስፋት እንዲሰጥም ፖሊሲ አውጥተው ተግብረዋል። በዓለም ትልቁ የተባለውን የመንግስት የጤና መድህን ፕሮግራም በመቅረጽ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ድሆች ነፃ ህክምና እንዲያገኙ ማደረጋቸውም በሰፊው ሕዝብ በኩል ስማቸውን የሚያስነሳ ግብር ሆኖሏቸዋል።

በአገሪቱ ለሕገ ወጥ ገንዘብ ዝውውር እና ሕገ-ወጥ የውጭ ምንዛሪ ምቹ ሁኔታ ፈጥሮ የነበረው ባለ500 እና ባለ1000 ሩፒ እንዲቀር ያወጁት በአንድ ምሽት ነበር። ምንም እንኳን በተሰጠው አጭር ጊዜ ለመቀየር ረጃጅም የባንክ ሰልፎች ቢፈጠሩም ቅሉ፣ ይሄ ጠንካራ ውሳኔያቸው ሩፒን ከመውደቅ አደጋ ጠብቆታል። ሕንድን በዲጂታል ክፍያ በዓለም ቀዳሚ ያደረጋት ሕንድ ስታክ ተብሎ የሚጠራውን ሥርዓትም ያስጀመሩት ‘ርሳቸው ናቸው። ይኸ ዲጂታል ሥርዓት ዛሬ በሕንድ ከተሞች ያሉ ከአንድ ቢሊየን የማያንሱት ነዋሪዎች፣ ከብርጭቆ ሻይ እስከ ትላልቅ የገበያ ማዕከላት የንግግድ ልውውጥ ድረስ በስልካቸው ክፍያ ይፈጽሙበታል። በመሠረተ-ልማቱም ቢሆን፣ በሕንድ አውድ አብዮት ተደርጎ የሚወሰድ ስር ነቀል ለውጥ አስመዝግበዋል። በየቀኑ የሚገነባው የሀይዌይ መንገድ ርቀት በከፍተኛ ሁኔታ ጨምሯል፤ አዳዲስ ዘመናዊ ባቡሮች ስራ ከመጀመራቸው ባሻገር፣ የፈጣን ባቡር ፉርጎዎችንም በየቀኑ ማምረት ጀምረዋል። በህዋ ሳይንስም ቢሆን፣ አገራቸውን በዝቅተኛ ወጪ የጨረቃን ደቡባዊ ዋልታ የረገጠች የመጀመሪያዋ አገር አድርገዋታል።

ወታደራዊ ቁሳቁሶችን ከውጭ ማስገባትን በመቀነስ በአገር ውስጥ ማምረት ላይ ትኩረት ያደረጉት ሞዲ፣ የመጀመሪያው የአውሮፕላን ተሸካሚ መርከብ በቀጥተኛ ተሳትፏቸው ስለማሰራታቸውም ይነገርላቸዋል። የራሷን የቺፕ ማምረቻ ኢንዱስትሪ ለመገንባት ቢሊዮን ዶላሮችን የመደበችው የሞዲ ሕንድ፣ እንደሚጠበቀው ይሄ ቴክኖሎጂ ከተሳካላት አገሪቱ ካለችበት አኹናዊ ሁኔታ በብዙ ደረጃ ያስፈነጥራታል ተብሎ ይጠበቃል።

ወደ ምሥራቁም፣ ወደ ምዕራቡም የሚያማትሩት ሞዲ፣ በውጭ ጉዳይ ፖሊሲያቸው ከአሜሪካ እስከ ሩሲያ፣ ከአውሮፓ ኅብረት እስከ ብሪክስ በመተጣጠፍ፣ አገራቸውን የመሃል ተጫዋች አድርገዋታል። በቡድን 20 የቱጃር አገራት ወቅታዊ ፕሬዝዳንትነቷ ወቅትም፣ የአፍሪካ ኅብረት የቡድኑ ቋሚ አባል እንዲሆን በማድረግ ታላቅ ዲፕሎማሲያዊ ድል ስለማስመዝገቧ ያተቱ ዘገባዎችም፣ ውዳሴውን የጀመሩት የሞዲን ስም ከፊት አድርገው ነበር። ከቻይና ጋር በድንበር ጉዳይ ፀበኛ ቢሆኑም ቅሉ፣ ልዩነታቸውን አቻችለው የብሪክስ መስራች አገር መሪ መሆናቸው ዲፕሎማሲያዊ መተጣጠፋቸውን ያሳየላቸው ተብሎላቸዋል። እነሆ እኒህ እና ሌሎች የዘመነ-መንግስታቸው ስኬቶች ተደማምረው፣ ሰውየው ናሬንድራ ሞዲን፣ ከዲሞክራሲ አገራት መካከል ረጅም ጊዜ ቢመሩም፣ በሕዝባቸው ዘንድ ስማቸው ዛሬም ብዙ እንዳይቀዘቅዝ አድርጓቸዋል።

እንግዲህ ታላቋ ሕንድ፣ የክርስትና ስር በሌለበት ዲሞክራሲን ማቆም አይቻልም የሚለውን የምዕራቡን መማሪያ መጻህፍት እየፈተነች፣ በራሷ ቅርጽ ዲሞክራሲዋን እያበጀች እዚህ ደርሳለች። የመጨረሻ የሥልጣን ዘመናቸው እንደሆነ የሚታመነውን ቀጣዮቹን አራት ዓመታትም፣ ከጾመኛው ሞዲ ጋር ትስነብታለች። ኢትዮጵያም፣ ከዚያ ባለ ብዙ ብሔር እና ሃይማኖት አገር፣ የጀመረችውን ዲሞራሲን የማቆም መውተርተር እንዴት ስር ማስያዝ እንደምትችል ትማራለች ብለን ተስፋ እናደርጋለን።

## ፍካሬ ዘ እንደራሴ

"እንደራሴ" የሚለው ንባበ-ቃል በኢትዮጵያ ጥንታዊ እና ዘመናዊ የፖለቲካ ተዋስዖ እና የሥነ-መንግሥት ታሪክ ውስጥ ግዝፈት የነሳ ፍካሬያዊ ንባበ-ቃል ነው። የቃሉ ከየት መጥነት እና ፍካሬም፣ በአጠቃሎ መልኩ ይኽን መሰል ፍቺዎች ነበሩት/አሉትም።

ንባበ-ቃሉ የተገኘው "እንደ" እና "ራሴ" ከሚሉ የኹለት ቃላት ጥምረት ነው። "እንደ"፦ መስያ፣ ፈንታን ወይም ምትክን ሲያመለክት፤ "ራሴ"፦ ራስ ጠሪውን ማንነት አልያም ባለቤቱን-ሲፈከርም ባለሥልጣኑን ያነጽራል። በአማሪያዊ ፍቺውም፣ "እንደ እኔ" ወይም "እኔን ሆኖ" ማለት ነው ይሏል። በኢትዮጵያ ሥነ-መንግሥት ታሪክ "እንደራሴ" የሚለው ማዕረግነቱን ሲያጣቅስ፣ በተለያዩ ዘመናት የተለያየ ማኅበረ-ፖለቲካዊ ትርጓሜ ነበረው፤ ለማሳያ፦

ሀ- የንጉሠ ነገሥቱ ተወካይ (በፈረንጅ አፍ- Regent እንዲሉ)፦ በንጉሣዊው ሥርዓት ዘመን ንጉሠ ነገሥቱ በአንዳች ምክንያት (ለዐቅመ-መንበር ባለመድረስ፣ በሕመም ወይም በሌላ ምክንያት) አገረ-መንግሥቱን መምራት ካልቻሉ፣ ሙሉ ሥልጣን ተሰጥቶት አገሪቱን የሚያሥተዳድረው ሰው "ቢትወደድ-እንደራሴ" ይባል ነበር።

ለ- የአካባቢ ወይም የክፍለ-ሀገር ገዢነት፦ ንጉሠ ነገሥቱ በየክፍለ ሀገራቱ 'ራሳቸው ዘወትር መገኘት ስለማይችሉ፣ በ'ርሳቸው ስም የሚፈርዱ እና የሚያሥተዳድሩ ተወካዮቻቸውን "እንደራሴ" ይሏቸዋል፤ ይኽም የንጉሡ ምሉዕ ተወካይነትን ይሰጣል።

ሐ-የሕዝብ እንደራሴነት፦የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ሕገ-መንግሥት ከመጣ ወዲኽ ግን ቃሉ አዲስ ፍካሬ ያዘ። ሕዝቡ በ'ራሱ ፈንታ ሆኖ በምክር ቤት እንዲመክርለት እና ውሳኔም እንዲሰጥለት የሚመርጣቸው ሰዎች "የሕዝብ እንደራሴዎች" መባል ጀመሩ። የዚኽ ፍካሬም፣ "ሕዝቡን ሆኖ የሚሠራ"፣ "ምስለ-ሕዝብ" አልያም "የሕዝቡ ተወካይ" የሚል ትርጓሜን አሰጠው።

ዛሬ "ተወካይ" (በምዕራቡ የምክር ቤት ታሪክ ጅማሮ-Representative-እንዲሉ) ከሚለው ቃል ጋር መሳ ለመሳ ሆኖ ያገለግላል። ሆኖም "እንደራሴ" የሚለው ቃል ከውክልና ባለፈ፣ የወከለውን አካል ሙሉ ክብር እና ማንነታዊ ተዛምዶ ይዞ የሚገኝ ክብደት ያለው ፖለቲካዊ እና ማኅበረ-ባህላዊ ፍካሬ አለው።

## የብሪጅ አፈካከር

ተቋማችን ብሪጅ፣ የአማርኛን ሰዋስው ደንብ ጠብቃ፣ ይኽንን ቃል ከኋለኛው ወደዚኽ ዘመን አናጥቃ በመፈከር ተጠቅማለች። አስቀድመን ሊቃውንቱ ያስቀመጡትን እንጥቀስ፤ ደስታ ተክለ ወልድ፣ እንደ ራሴ፣ እኔን ሆኖ፣ የእኔን ሥልጣን ይዞ የሚሠራ ብለው ሲፈቱት፤ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ፣ በፈንታ፣ በምትክ የሚቆም ሲሉት፤ ተሰማ ሀብተ ሚካኤል ግጸው በተራቸው፣ ተለዋጭ፣ ተወካይ፣ ባለሙሉ ሥልጣን የሚል ፍቺ ይሰጡታል። ማኅተመ ሥላሴ ወልደ መስቀልም ቢሆኑ፣ አንድ ሰው በራሱ ስም ሳይሆን በሌላው ስም ተገኝቶ የሕግ ተግባራትን ሲያከናውን እንደራሴ መባሉን ያነሳሉ። እነዚኽ ዋቢዎች እንደሚያሳዩት፣ ቃሉ በመጀመሪያ ለነገሥታት ተወካዮች ብቻ ይሠራበት የነበረ ሲሆን፣ ኋላ ለሕዝብ ተወካዮች እንዲሠራበት የተደረገው የሕዝቡን ልዕልና ለመግለጽ ውለዋል፤ አለፍ ሲልም፣ ተወካዩ ሕዝቡን ሆኖ ይገኛል፤ እንደ ሕዝቡ ሆኖ ይጠራል የሚለውን ፍካሬ ይሰጣሉ።

በዚኽ አግባብ፣ "እንደራሴ" ስንል፦ አንድም ራስ የሚለውን የኢትዮጵያ ፌዴሬሽን ከቆመበት 'የራስን ዕድል በራስ የመወሰን' ሕገ-መንግሥታዊ ነባር መርህ ጋር አናጽረን ፈክረነዋል። ይኽ ማለት፣ በዚኽ መርህ ውስጥ ያለው 'ራስ'፣ የሚለው ትርጉም የሚጠቅልላቸውን ብሔር፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች፣ በ "እንደራሴ" ውስጥ ያለውን 'ራሴ'ን ለመፍታት ፍካሬያዊ ትርጓሜን ተጠቅመናል። ከዚያ ባለፈም፣ በቀደመው ዘመን መራጩ ንጉሠ ነገሥቱ እንደሆነው ሁሉ፣ በዚኽኛው የእኛው ዘመን ሕዝብ ነውና፣ "እንደራሴ" ስንል፦ እንደ መረጠው ሕዝብ፣ ብሔረሰብ አልያም ብሔር የሆነ በሚል ፍቺ መጠቀማችንን ልብ ይሏል። በዘመናዊው የምርጫ ሥርዓት ስናነጽረውም፣ መራጩ ግለሰብ እንደራሴውን 'ተናገር በከንፈሬ፣ ተቀመጥ በመንበሬ' ሲል፣ በነገረ-ሕይወቱ ይወስንለት ዘንድ ወደ ምክር ቤቱ መርጦ ይልከዋል። የመረጠውም እንደራሱ ካልሆነለት፣ ምስለ እኔነቱን ሊነጥቀው መቻሉን ያስረግጣል።

የ"እንደራሴ" ንባበ-ቃል፣ ምንም እንኳን የመጀመሪያው የኢትዮጵያ የእንደራሴዎች ምክር ቤት ሲቋቋም፣ የምክር ቤቱ የሥራ ቋንቋ በዘመኑ ብሔራዊ ቋንቋ የነበረው አማርኛ ብቻ ቢሆንም ቅሉ፣ ንባበ-ቃሉ ግን በሌሎቹ የአገራችን የብሔር ብሔረ ሰቦች ቋንቋዎች ውስጥም መገኘቱን ልብ ይሏል፤ ለማሳያ፦ በሲዳማ- amaalete mina፣ በአፋን ኦሮሞ-Bakka bu'aa፣ በትግሪኛ- ከማይ፣ በወላይተኛ Kal Ati-ya/Taga ton መባሉን ያስታውሷል።

**ከራስ ውርድ፦**

"በእነዚኽ ወርኃዊ የእንደራሴዎቹ ጥቅንሮች ውስጥ ያሉት ኹሉም የገጸ-ሰብ እና የገጸ-መስኮች ምስሎች የተገኙት ከሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጽሕፈት ቤት ይፋዊ የመረጃ ምንጮች ነው፤ እንዲኹም፣ ኹሉም ቁጥራዊ ዘገባዎች የተወሰዱትም ከዚኽ ምንጭ ነው። ዳሰሳዊ ምልከታዎቹ፣ አጠቃሎዎች እና ተያያዥ ትንታኔዎቹ የተቋማችን ናቸው።"

# እንደራሴ

እንደራሴ በብሪጅ ሪሰርች እና ኢኖቬሽን በየወሩ እየተዘጋጀ ይቀርባል።

**BRIDGE** Research & Innovation for Democratic Governance and Enhanced Peace

+251 115 57 74 96

+251 911 86 12 34

research@bridge-et.org

https://bridge-et.org/

150096, Addis Ababa, Ethiopia.

Kazanchis, across the main gate of UNECA, SA Building, 9th Floor, Office No. 5, Addis Ababa.